ስዕላት

ቅዱሳን ስዕላት በመጽሐፍ ቅዱስ

አንዳንዶች መንፈሳዊውን ልምምድ ከጣዖት አምልኮ በማደበላለቅ በዓይነ ሥጋ እየመዘኑ ስለሚረዱ ፥ እውነትን ከመገንዘብና ከመቀበል ይልቅ አምልኮ ነው ሲሉ ይሰማሉ ። እውነት በቅዱሳን ስዕላት ፊት መስገድ ለጣዖት መስገድ ነውን እስቲ ቅዱስ ቃሉን መሰረት በማድረግ እንመልከት፦

ለቅዱስ ስዕል ስንሰግድ ለፍሬሙ አልያም ለወረቀቱ ለቀለሙ አይደለም እምንሰግደው ለስዕሉ ባለቤት እንሰግዳለን።

ሙሴ በእግዚያብሔር ታዞ ኩሩቤልን(መላእክትን) ሰርቶ ነበር በታቦቱ ግራ እና ቀኝ ይቀመጥ ነበር እና እስራኤላዊያን ለታቱ ሲሰግዱ ታቦቱ ለተሰራበት ግራር(እንጨት)አይደለም የሚሰግዱት በታቦቱ ላይ ለሚያድረው እግዚያብሔር ነው ይህን ከተረዳን እኛም ለስዕል ስንሰግድ ለስዕሉ ባለቤት የሚሰገድ ነው

ለታቦት ስንሰግድ ለእንጨቱ አንሰግድም ለባለቤቱ እንሰግዳለን እንጂ!!!

ለስዕል ስንሰግድ ለወረቀቱ አይደለም ለባለቤቱ እንሰግዳለን እንጂ!!!

ለኢየሱስ ክርስቶስ፤ለድንግል ማርያም፤ለመላእክታት፤ለቅዱሳን፤ለሰማእታት ስዕል ስንሰግድ ለወረቀቱ ለፍሬሙ አልያም ለቀለሙ አይደለም እምንሰግደው ለስዕሉ ባለቤት እንጂ!!!!

ተራ የመሰሉ ነገሮች በእምነት ታላቅ ናቸው! ድንቅ ተአምራትን የፈጸመች የሙሴ በትር ተራ እንጨት አትሆንበትም (ዘጸ 4:12)፤ ባህር የከፈለች የኤልያስ መጎናጸፊያንም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ኃይል አድርጎባታልና በተራ ጨርቅ አይመለከታትም (2 ነገ 2:8)፤ ብረት ከባህር እንዲያወጣ ነቢዩ ኤልሳዕ የተጠቀመበት ቁራጭ እንጨት (2 ነገ 6:5-7) ፥ የቅዱስ ጳውሎስ የልብስ እራፊ (ሥራ 19:11) ፥ የቅዱስ ጴጥሮስ ጥላ (ሥራ 5:15)... እግዚአብሔር የፈውስና የተአምራት መግለጫው አድርጓቸዋልና በሥጋዌ ዓይን እየመዘንን የተፈጥሮ ባህርያቸውን በመዘርዘር ጥርጣሬንና ክህደትን የምንፈጥርባቸው አይደሉም ። ይልቁንም ከነዚህ ማስረጃ ምሳሌዎች የምንረዳው ቅዱሳን የነፍሳቸው ቅድስና ለሥጋቸው ፥ የሥጋቸው ቅድስና ለምርኩዛቸው ፥ ለአልባሳታቸውና ጥላቸው ተርፎ ድንቅ ተአምራትን ማድረጉን ነው ። በዚሁ መሰረት ቅድስናቸው ለስዕሎቻቸውም የተረፈ በመሆኑ በስዕሎቻቸው ተአምራትን እንደሚያደርጉ ጸጋው የደረሳቸው ክርስቲያኖች ምስክሮች ናቸው ።ነቢዩ ኤልያስ ካረገ በኋላ ደቀ መዝሙሩ ኤልሳዕ በኤልያስ መጎናጸፊያ ተአምራትን አድርጎአል (2 ነገ 2:14) ። ይህም ማለት ቅዱሳን በአጸደ ሥጋ አጠገባችን ባይኖሩም በተሰጣቸው ጸጋ ፥ በስዕሎቻቸውም ሆነ በሌላ ንዋየ ቅዱሳት

እንደሚራዱን የሚያስረዳ ነው ። ሥርዓቱን ያስጀመረው እርሱው አምላካችን ስለሆነ ስዕልን ከፊት አድርጎ እርዳታን ለማግኘት በህሊና መጸለይ ርኩሰትና እግዚአብሔርን መክዳት አይባልም ።

ኢኮኖማህያ ስእልን የሚያመልኩ ናቸው። ኢኮኖላትርያ ስእልን የሚያቃጥሉ ናቸው። እኛ ግን ስእልን አናመልክም ስእልን አናቃጥልም! በአግባቡ እናከብራለን! ዋናው እምነት ነው! ተራ የሚመስሉ ነገሮች በእምነት ዋጋ አላቸውና!

1. ለመጀመሪያ ጊዜ ስዕልን የሰጠው እግዚአብሔር ነው።

ዘፍ. 1 ÷ 26-27

እግዚአብሔርም፡አለ፦ሰውን፡በመልካችን፡እንደ፡ምሳሌ
ያችን፡እንፍጠር፤የባሕር፡ዓሣዎችንና፡የሰማይ፡ወፎች
ን፥እንስሳትንና፡ምድርን፡ኹሉ፥በምድር፡ላይ፡የሚንቀ
ሳቀሱትንም፡ኹሉ፡ይግዙ።
እግዚአብሔርም፡ሰውን፡በመልኩ፡ፈጠረ፤በእግዚአብሔር፡መልክ፡ፈ
ጠረው፤ወንድና፡ሴት፡አድርጎ፡ፈጠራቸው።

2. ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መልኩ የተናገረው

ማቴ. 22 ÷ 19-21

የግብሩን፡ብር፡አሳዩኝ፡አለ።እነርሱም፡ዲናር፡አመጡ
ለት።
ርሱም፦ይህች፡መልክ፡ጽሕፈቲቱስ፡የማን፡ናት፧አላቸው።
የቄሳር፡ነው፡አሉት።በዚያን፡ጊዜ፦እንኪያስ፡የቄሳርን፡ለቄሳር፡የእግዚ
አብሔርንም፡ለእግዚአብሔር፡አስረክቡ፡አላቸው።

ይህች መልክ ሲል ለጊዜው የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ ሲል ለፍጻሜው ግን ይህች ስዕል ሲል የቄሳርን መልክ ለማለት ነው። ቄሳር ምንድን ነው? ሰው ነው ። ሰው የማን መልክ ነው? የእግዚአብሔር መልክ ነው።

3. ስለ ስዕል በብሉይ ኪዳን

ዘጸ. 25 ÷ 18-22

ሁለት፡ኪሩቤል፡ከተቀጠቀጠ፡ወርቅ፡ሥራ፥በስርየት፡መ
ክደኛውም፡ላይ፡በኹለት፡ወገን፡
ታደርጋቸዋለኽ።ከስርየት፡መክደኛውም፡ጋራ፡አንዱን፡
ኪሩብ፡ባንድ፡ወገን፥ኹለተኛውንም፡ኪሩብ፡በሌላው፡ወ
ገን፡አድርገኽ፡ባንድ፡ላይ፡ትሠራዋለኽ።
ኪሩቤልም፡ክንፎቻቸውን፡ወደ፡ላይ፡ይዘረጋሉ፥የስርየት፡መክደኛውን
ም፡በክንፎቻቸው፡
ይሸፍናሉ፥ፊታቸውም፡ርስ፡በርሱ፡ይተያያል፤የኪሩቤል
ም፡ፊቶቻቸው፡ወደ፡ስርየት፡መክደኛው፡ይመለከታሉ።
የስርየት፡መክደኛውንም፡በታቦቱ፡ላይ፡ታደርገዋለኽ፤
እኔም፡የምሰጥኽን፡ምስክር፡በታቦቱ፡ውስጥ፡
ታኖረዋለኽ።በዚያም፡ከአንተ፡ጋራ፡እገናኛለኹ፤የእስ
ራኤልንም፡ልጆች፡ታዝዘንድ፡የምሰጥኽን፡ነገር፡ኹሉ
፥በምስክሩ፡ታቦት፡ላይ፡ባለው፡በኹለት፡ኪሩቤል፡መካ
ከል፥በስርየት፡መክደኛውም፡ላይ፡ኾኜ፡እነጋገርኻለኹ።

ርዝመቱም፡ኹለት፡ክንድ፥ወርዱም፡አንድ፡ክንድ፥ቁመቱ፡አንድ፡ክንድ፡ ተኩል፡የኾነ፡ገበታ፡ከግራር፡ዕንጨት፡ሥራ።በጥሩም፡ወርቅ፡ትለብጠ ዋለኽ፤በዙሪያውም፡የወርቅ፡አክሊል፡አድርግለት፤

ዘሁ.21 ÷ 8-9

ሙሴም፡ስለ፡ሕዝቡ፡ጸለየ።እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡-እባብን፡ሠርተ ኽ፡በዐላማ፡ላይ፡

ስቀል፤የተነደፈውም፡ኹሉ፡ሲያያት፡በሕይወት፡ይኖራል፡አለው።

ሙሴም፡የናሱን፡እባብ፡ሠርቶ፡በዐላማ፡ላይ፡ሰቀለ፤እ

ባብም፡የነደፈችው፡ሰው፡ኹሉ፡የናሱን፡እባብ፡ ባየ፡ጊዜ፡ዳነ።

ዬሐ. 3 ÷ 14-15

ሙሴም፡በምድረ፡በዳ፡እባብን፡እንደ፡ሰቀለ፡እንዲሁ፡

በርሱ፡የሚያምን፡ኹሉ፡የዘለዓለም፡ሕይወት፡እንዲኖረ

ው፡እንጂ፡እንዳይጠፋ፡የሰው፡ልጅ፡ይሰቀል፡ይገባዋል።

4. ስለ ስዕል በአዲስ ኪዳን

ገላ. 3 ÷ 1

የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?

ዬሐ. 3 ÷ 14

ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።

ዘኍ.21 ÷ 8-9

ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ። እግዚአብሔርም ሙሴን፦ እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል አለው።

ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ።

ቅዱሳት ስዕላት ለቤተክርስቲያናችን ምን ይጠቅማሉ?

የክርስትና እምነትን ይሰብካሉ።

ሀይማኖታዊ ምስጢራትን ያስታውሳሉ።

በስዕሉ ላይ ያሉትን ቅዱሳንን እየተመለከትን በሕይወታችን እንመስላቸዋለን።

ውስጣችን ይመሰጣል ሰማያዊ ነገርን እናስባለን።

ስለ ቅዱሳት ሥዕላት››››(ተከታታይ ትምህርት ክፍል-29)

ሥዕል አምልኮተ እግዚአብሔርን በሚያውቁ በጥንት እስራኤላዊያን ዘንድ እና ድንጋይ ጠርበው እንጨት አለዝበው ጣዖታትን ሠርተው በሚያመልኩ አሕዛብ ዘንድ የአምልኮት

መገለጫ እንደነበር ታሪክ የዘገበው እውነት ነው። ይሁን እንጂ የአሕዛብ ቅርጻ ቅርጽ በእግዚአብሔር ዘንድ የነቀፉ ቢሆንም በእሥራኤል ዘንድ የነበሩት ቅርጻ ቅርጾች ግን ከራሱ ከእግዚአብሔር የተፈቀዱ በመሆናቸው እንደ አሕዛብ ጣዖታት የማይነቀፉ የአምልኮት መገለጫዎች ናቸው። ለዚህም ማስረጃ ዘፀ 25÷19-20 ፣ መፍሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 6÷23-28 እና ሕዝቅኤል 9÷3 መመልከት እንችላለን። በእነዚህ ምዕራፍና ቁጥሮች ላይ እግዚአብሔር ራሱ ለሙሴ ‹‹ሥዕለ ኪሩብን›› እንዲሰራ እንዳዘዘው እንመለከታለን። ይህንም መሠረት በማድረግ ዛሬም ሥዕለ ኪሩብ በታቦተ ሕጉ ላይ ይሳላል። ስለዚህ ቅዱሳት ስዕላትን እንድንቀበል አዛዙ እግዚአብሔር መሆኑን አስተውል።

+++ስለ ሌሎች ቅዱሳት ስዕላት ግን በቤተክርስቲያን የተጀመረበት ለየት ያለ ምክንያት አለው :: የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ትምህርታቸውን ያስፋፉት ዋሻ ፈልፍለው ጉድጓድ ቆፍረው በፍርክታ እና በግበበ ምድር(ካታኮምቡ) ውስጥ ነው። በነዚህ ዋሻ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በስዕላዊ መግለጫ እያስደገፉ ያስተምሩ ነበር። የክርስቶስን ስቅለትና የመከራ ገጽታ እንዲሁም የእናቱን የመከራ ቀን አኳኋን እየሳሉ አንዳቸው ለአንዳቸው ወንጌልን ይሰባበኩ ነበር። ምክንያቱም በዛን ወቅት በሮማውያን ህግ ወንጌልን ቆሞ መስበክና ስለ ክርስቶስ መናገር አንገትን ያስቀላ ስለነበር ነው። በተጨማሪም ስለ ሃይማኖታቸው ሲሉ በዐላውያን ነገሥስታት ሰይፍ የወደቁትን ሰማዕታት ከነአሟሟታቸው በሥዕል ለመታሰቢያነት ያኖሩ ነበር።በዚህ አኳኋን ክርስቲያኖች እምነታቸውን የሚገልፁባቸውን ቅዱሳት ስዕላት በአክብሮት በመያዝ እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ቆየ። ነገር ግን በሥዕል ምክንያት በሮምና በቤይዛንታይን ግዛት በሚኖሩ ክርስቲያኖች ዘንድ አለመግባባት ተፈጠረ። እነዚህ ሁለት ወገኖች

1ኛ. ኢኮኖላትሪያ (ስዕልን የሚያመልኩ)

2ኛ. ኢኮኖማኻያ (ስዕልን የሚጠሉ) ናቸው።

ለሁለቱ ወገኖች አለመግባባት ዋናው ምክንያት ኢኮኖላትሪያ ሥዕልን ከመውደዳቸው የተነሣ ቅዱሳት ስዕላትን አማልክት ናቸው እስከማለት በመድረሳቸው ሲሆን ኢኮኖማኻያ ደግሞ ፀረ ስዕል አቋም በመያዝ እንደውም ቅዱሳት ስዕላት መጥፋት አለባቸው በማለት ለመነሣታቸው ነው። በነዚህ ወገኖች መካከል አለመግባባት ከመኖሩ የተነሳ ፀባቸው እየከረረ በመምጣቱ የሁለቱንም ክፍሎች ሃሳብ በሚጣጣም መልኩ የሚዳኝ አንድ ጉባዔ በ748 ዓ.ም ተደረገ። ጉባኤውም ቅዱሳት ስዕላት እንዳይመለኩና እንዳይቆሸሹ ውሳኔ አስተላለፈ::ነገር ግን ለቅዱሳት ስዕላት ክብርና እንክብካቤ እንዲሁም ለስዕሉ ባለቤት ስግደት እንደሚገባ ቀኖና ሰራ። ልብ ልንለውና ልናስተውለው የሚገባን አንድ

እውነት ቢኖር በሥዕል ፊት ቆሞ መፀለይ ከባለ ስዕሉ ረድኤት በረከትና ምልጃ ለማግኘት እንጂ ወረቀቱን ማክበራችን ወይም መለመናችን አይደለም። ለምሳሌ በጌታ ስዕል ፊት መፀለያችን ለባለ ስዕሉ ለጌታ መጸለያችን ነው እንጂ ለወረቀቱ አይደለም። ደግሞም በፍቅርና በእምነት የሚሆን ነገር ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ባይጻፍ እንኳን ያጸድቃል እንጂ አያስኮንንም!!!

+++"የተቀረፀውን ምስል ለአንተ አታድርግ" ዘፀ 20÷4 የሚለውን በመጥቀስ ብዙዎች አነስተኛ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀታቸውን በመጠቀም ይሄ ቃል ለቅዱሳት ስዕላት ፣ ለታቦታት እና ለመስቀል እንደተነገረ አድርገው ሲያቀርቡ ይሰማል።ይህ ግን የእነርሱን የዕውቀት ማነስ የሚያሳይ እንጂ ታቦት መስቀልና ስዕላት ጣዖታት ሆነው ለእነርሱ እትስገዱ አታክብሯቸው የሚል አንድምታ የለውም። "ታቦትን ከግራር እንጨት ስራ" ዘዳ 10÷1-5 ያለው እግዚአብሔር አይደለም እንዴ? እንግዲህ እግዚአብሔር የተቀረፀ ምስል አታድርግ ካለ በኋላ ታቦትን እንዲሰራ ማዘዙ ጣዖትን አምልክ ማለቱ ይሆን? መስቀልም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስላምን ለሰው ልጆች ለማደል የተሰቀለበት ክቡር ደሙ የፈሰሰበት ቅዱስ ሥጋው የተቆረሰበት ክቡራት እግሮቹ የተቸነከሩበት የጌታ ዙፋኑ ነው እንጂ እንደጣዖት ማየት አዕምሮ ላለው ሰው ተገቢ አስተሳሰብ ነው ብለን አናምንም!!! ስዕላት ደግሞ የተቀረፁ ምስሎች አይደሉም የሚዳሰሱና የሚጨበጡም አይደሉምና።

+++ታዲያ የተቀረጹ ምስሎች የተባሉት እነማን ናቸው? ቢባል "የአሕዛብ ጣዖታት የብርና የወርቅ ፤ የሰው እጅ ሥራ ናቸው አፍ አላቸው አይናገሩም ዓይን አላቸው አያዩም ፣ ጆሮ አላቸው አይሰሙም ፣ እስትንፋስም በአፋቸው የለም የሚሰሩአቸው ሁሉ የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁኑ" መዝ 134 (135) 15-18 የተባሉትን ነው። በመሆኑም በቅዱሳንና በጻድቃን ስዕል ፊት ቆመን የምልጃ ጸሎት ማቅረባችን የሚያስነቅፍ ሳይሆን ይልቁንም ቅዱሳን ያለንን ክብርና ፍቅር የሚገልፅ ነው። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ "እናንተ የማታስተውሉ የገላቲያ ሰዎች ክርስቶስ በፊታችሁ እንደተሰቀለ ሆኖ ተስሎላችሁ ነበር? ለእውነት እንዳትታዘዙ ማን አዚም አደረገባችሁ?" ገላ 3÷1-2 በማለት ስዕላት ምን ያህል የአምላኪውን አዕምሮ ለአምልኮት ዝግጁ እንደሚያደርጉት የገለፀው።

+++አንዳንዶች የጌታንና የእመቤታችንን ስዕል እውነተኛ የእነርሱ ነው ወይ? በማለት በጥርጥር ማዕበል ሲዋዥቁ ይስተዋላሉ ለነዚህ ተጠራጣሪዎችና ለሌሎችም የጌታችንና የእመቤታችን ስዕሎች እንዴት እንደተገኙ ታሪካዊ ማስረጃ ቀርቧልና ያንን አቅርቤዋለሁ።

+++ለመጀመሪያ ጊዜ የጌታን ሥዕል የሳለው ወንጌላዊው

ቅዱስ ዮሐንስ ነው :: ሥዕሉንም የሳለው ከ14-37 ዓ.ም ሮምን ይገዛ ለነበረው ለጠባርዮስ ቄሳር ነው። ጌታም የተሰቀለው በእርሱ ዘመነ መንግሥት ነበር። ይህ ንጉሥ በጣም የሚወደው አንድ ልጅ ነበረው። እሱም ሞተበት። በልጁ ሞት በጣም አዝኖ ስለነበር ሬሳውን ሳያስቀብር ሰነበተ ከጥቂት ቀን በኋላ ጌታ በኢየሩሳሌም ያደርግ የነበረውን ተአምራት ያውቅ ስለነበር "ከጢባርዮስ ቄሳር ምድራዊ ንጉሥ የተላከች መልእክት ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ትድረስ" ብሎ ልጁን እንዲያስነሣለት የምልጃና የልመና ጽሑፍ ጽፎ ከልጁ ሬሳ ጋር ወስደው ጎልጎታ (የጌታ መቃብር) ላይ እንዲያኖሩለት ባለሟሎቹን ላከ። እነርሱም ሄደው ደብዳቤውንና ሬሳውን በጌታ መቃብር ላይ ሲያኖሩት ሬሳው አፈፍ ብሎ ተነሥቷል። ጢባርዮስም ከደስታው ብዛት የተነሣ የጌታን ውለታ ለመክፈል የዚህን ሰው እናቱን አምጡልኝ? እኔ ቋሚ ለጓሚ ፣ ሚስቴ ደግሞ ገረድና ደንገጡር ሆና እናገለግላታለን ብሎ ወደርሷ መልእክተኛ ቢልክ የድንግል ማርያም ክብር ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ስላልሆነ ተሰውራባቸው አላገኟትም። ጢበርዮስ ቄሳር ግን ተስፋ እንዳይቆርጥ ወንጌላዊው ቅዱስ ዬሐንስ በዕለተ አርብ በመስቀሉ ላይ እንዳየው አድርጐ ከለሜዳ አስታጥቆ ጌታን ስሎለታል :: ዮሐንስ ስዕሉን ስሎ እንደጨረሰ "አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደ ሰቀሉኝ አንተ ደግሞ ሁለተኛ እርቃኔን ሰቀልከኝን?" የሚል ድምጽ ከስዕሉ ወጥቶአል ይህም የስዕሉን እውነተኛነት ማረጋገጫ ሆኗል። ዛሬም ድረስ የጌታ ስነስቅለት ስዕል የሚሳለው የዮሐንስን ስዕል አብነት በማድረግ ነው :: እኛም ለቅዱሳት ስዕላት ያለን አክብሮት የመነጨው ከዚህ እውነታ በመነሣት ነው።

+++ሌላው የጌታ ስዕል ምንጭ ጲላጦስ ለጢባርዬስ ቄሳር ስለጌታና ስለ እናቱ ድንግል ማርያም የላከው ስዕላዊ መግለጫ ነው። መልእክቱም የሚከተለው ነው።

"ለጢባርዮስ ቄሳር ስላም ላንተ ይሁን ኢየሱስ ስለሚባለው ሰው ግርማዊነትህ ለማወቅ የጠየቅኸውን ለማሟላት ከዚህ የሚከተለውን እጽፍልሀለሁ። በዚህ እኔን እንደራሴ አድርገህ በሾምኸኝ በፍልስጤም ምድር እጅግ በጣም የተለየ መልክና ሥልጣን ያለው አንድ ሰው ተነሥቷል። ታላቅ መምህርና ነቢይም ነው ይሉታል። ደቀመዛሙርቱ ግን የእግዚአብሔር ልጅ ነው ይላሉ :: ታላላቅ ተአምራትን እያደረገ ይገኛል። ሙታንን ያስነሳል ድውያንንም ከማናቸው ህመም ይፈወሳል ከዚህም ጋር ጥልቅና መንፈሳዊ በሆነ ትምህርቱ መላዋን ኢየሩሳሌም አስደንቋታል። አካሉ ግርማ ያለውና እጅግ ልዩ ነው አነጋገሩም የመጠቀና የእግዚአብሔር ጸጋ የተሞላበት በመሆኑ ማናቸውም የሚያየውና የሚሰማው ሁሉ ይማረክበታል :: አንዳንድ ጊዜ ብርሃናዊ መልኩና ረዘም ብሎ የሚታየው ጽህሙ የሚሰጠው ፍፁም ውበት በማንም የሰው

ልጅ ላይ ታይቶ የማይታወቅ ነው። መልአካውያን አይኖቹና የጥቁር ወርቃማ ጠጉሮቹም አወራረድ በሚሰጡት የተንጸባረቀ ውበት ማንም ሰው ቢሆን ለረጅም ጊዜ አተኩሮ ሊመለከተው አይችልም የሚመስለው ፍጹም እናቱን ነው። እርሷም ደግሞ በዚህ ክፍለ አገር በማንም ያልታየ ውበትና የትህትና መልክ ያላት ልዩ ሴት ናት። ቆራጥ ከባድና የሚያከራክሩ ንግግሮቹም በውስጣቸው የሚገኘው ፍጹም የሆነ የመንፈስ ልዕልናና የዕውቀት መጠናቸው ከታላላቅ አዋቂዎች ተብለው ከሚገመቱት ሰዎች እጅግ አድርጐ የራቀና የጠለቀ ምስጢር አላቸው። በተግሳፅና በእዝናት ጊዜም በጣም ኃይለኛ ነው። በማስተማርና በማጽናናት ጊዜ ደግሞ በጣም ትሁት ፣ ተወዳጅና ልብ የሚመስጥ ነው። ራሱን ሳይከናነብና መጫሚያ ሳይጫማ በእግሩ ይሄዳል። በሩቅ የሚያዩት አንዳንዶቹ ይሳለቁበታል። ወደ ፊቱ ሲቀርቡና ሲያዩት ግን በመንቀጥቀጥና በመፍራት ይሰግዱለታል። ማንም ቢሆን ሲስቅ አየሁት የሚል የለም። ነገር ግን ብዙዎች በተደጋጋሚ ሲያለቅስ አይተውታል። የቀረቡት ሁሉ ብዙ ፈውስና ተአምራት ማግኘታቸውን ይናገራሉ። አይሁድ ግን ገዢና ተገዢ ሁሉም በእኔና በአባቴ ፊት እኩል ናቸው ፤ ምንም ልዩነት የላቸውም ብሎ ስለሚያስተምር የግርማዊነትህ አጥፊ ሳይሆን አይቀርም በማለት እየመጡ ይነግሩኛል። ስለዚህ ጉዳይ አጢነህ የወሰንከውን ውሳኔ ብታዘኝ

ወዲያውኑ ትዕዛዝህ የሚፈጸም ይሆናል። ጤና ሁን ጲላጦስ ጲንጤናዊ ነኝ ፒ.ሎንቱሌ” በማለት ጽፏል። ይህም ደብዳቤ ዛሬ ድረስ በታሪክ አጥኚዎችና ጠበብቶች እጅ ይገኛል። (ይህ ከላይ ያነበብነው የጌታ ዝርዝር መልክ ከታች ከምትመለከቱት የጌታ እውነተኛ ስዕል ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው እጅግ ይደንቃል) ዛሬ የሚሳሉ የጌታችን ቅዱሳት ስዕላትም ካነበብነው እውነት የሚወስዱ ናቸው። የጌታን ስዕል የሳለው ዮሐንስ ወንጌላዊ ሲሆን የእመቤታችንን “ምስለ ፍቁር ወልዳ”ን የሳለው ደግሞ ቅዱስ ሉቃስ ነው። ይህ ስዕል(ቅዱስ ሉቃስ የሣላት ምስለ ፍቁር ወልዳ) ዛሬ ድረስ በጥንታዊቷ ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይገኛል።

+++ሌላውና ዋናው የቬሮኒካ ታሪክ ለስዕል ጥሩ መነሻ ነው:: ጌታ በዕለተ አርብ ደሙን እያንጠፈጠፈ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ጐልጐታ በሚወጣበት ጊዜ መስቀሉ ከብዶት ደሙ ዓይኑን ጋርዶት በላብ ተጠምቆ አይታ ልቧ በሐዘን ስለተነካ ከተከተሉተ ሴቶች አንድዋ ቬሮኒካ የፊት ማበሻ ፎጣ ወስዳ ፊቱን እንዲጠርግበት ሰጠችው። እርሱም ፊቱን አብሶ ሲመልስላት ገጹ በጨርቁ ላይ ታትሞበት ቀረ ::ከዘመናት በኋላ ከጨርቁ ላይ በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ወደ ወረቀት ታትሞ ለምእመናን ታድሏል(ከታች ባለው ስዕል ላይ ተመልከቱት)። ዛሬም ድረስ በተለያዩ ኦርቶዶክሳውያን ቤት ይህ እውነተኛው የክርስቶስን መልክና ገፅ የያዘ ስዕል

ይገኛል። ታዲያ ስዕሉን ብናምንበትና ለስዕሉ ባለቤት ብንሰግድ የኛ ስህተት ምኑ ላይ ነው? እንኳን የጌታችን ፣ የእመቤታችንንና የቅዱሳን ስዕላት ቀርቶ የነ እገሌ ፎቶ እንኳ ክብር ተሰጥቶት በየቤታችን ግድግዳ ላይ ይሰቀል የለም እንዴ? የነ እገሌ ፎቶ እቤታችን መሰቀሉ ባየናቸው ቁጥር እንድናስታውሳቸውና ሲሞቱም መታሰቢያ እንድናደርጋቸው ከሆነ የቅዱሳት ስዕላትም ዓላማ የምናያቸው ቅዱሳን ማሰብና በቃል ኪዳናቸው አብረውን እንዳሉ ለማሰብ አይደል? ይቀጥላል (ይቆየን)።

ሌሎች ቅዱሳን, ቅዱሳት ሥዕላት, ቅዱሳን ነቢያት, የኢትዮጵያ ሥነ ሥዕል

ሥዕለ ቅዱስ ዳዊት፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

በነገው ዕለት የሚከበረውን የሕዳር ጽዮን በዓልን ምክንያት በማድረግ የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ሊያንጽ አስቦ ያልተፈቀደለትን ነገር ግን እውነተኛ ማደሪያ ታቦት ስለሆነችው ጽዮን እና ስለ ነገረ ልደቱ ስለተገለጸለት ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ሥዕል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርቲያን ምን እንደሚመስል ከሥር እንመልከት።

ቅዱስ ዳዊት በእግዚአብሔር ዘንድ እንደልቤ ተብሎ የተነገረለት፣ በትሕትናው፣ በንስሐው የተመሰከረለት እንዲሁም በብዙ ሀብታት የሚታወቅ ነቢይ እና ንጉሥ ነበር። ይህ ቅዱስ ለረጅም ዘመናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥዕላቸው ያለመቋረጥ ተሥሎ ከሚገኙት ቅዱሳን መካከል ነው። ሥዕሉም በብራና፣ በግድግዳ እንዲሁም በገበታ ሥዕሎች ላይ ተሥሎ ይገኛል።

ለምሳሌ በጥንታዊነታቸው ከሚታወቁት አብያተክርስቲያናት መካከል በገነተ ማርያም ቤተክርስቲያን በ13 መ.ክ.ዘ. የግድግዳ ሥዕል፣ በአባ ገብረመስቀል እና ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ግድግዳ ላይ (14/15ኛው መ.ክ.ዘ.)፣ በጉንዳጉንዶ የሚገኝ የብራና ሥዕል (15ኛው መ.ክ.ዘ.)፣ 17ኛው መ.ክ.ዘ. ተአምረ ማርያም ብራና ላይ፣ 18ኛው መ.ክ.ዘ. መዝሙረ ዳዊት እና በIES (IES-3792) ከሚገኙት ገበታ ሥዕል በገና እየደረደረ የሚታዩት ሥዕሎች ለዚህ ማሳያ ናቸው።

ቅዱስ ዳዊት በቤተክርስቲያናችንም በስፋት በገና ሲደረድር ይሣላል። በዚህ የአሣሣል ጭብጥም ቅዱስ ዳዊት ለረጅም ዘመናት በቤተክርስቲያናችን የእርሱን ቅዱስ ሥዕል ለአገልግሎት ከቅዱስ መዝሙር በተጨማሪ ለአገልግሎት ስትጠቀምበት ኖራለች።

በገና ሲደረድር እንዳለው በብዛት የሚገኙ ባይሆንም ሌሎች ቅዱስ ዳዊትን ጭብጦች ተሥለው ለአገልግሎት ውለዋል።

ዳዊት ጎሊያድን በእግዚአብሔር ሲያሸንፈው

በዓለ እረፍታ ለማርያም ሥዕል ላይ እያረጋጋት በበገናው የሚታየው ሥዕል ለምሳሌ በተአምረማርያም እና በሴቶች ወገን ባሉ ግድግዳዎች ላይ ይታያል።

ዳዊት በጎችን እየጠበቀ እና ነቢዩ ሳሙኤል ቅዱስ ዳዊትን ሲቀባው፣ በቅዱስ ሚካኤል ድርሳን ላይ ደግሞ ቅዱስ ዳዊትን እንዲቀባው ቅዱስ ሚካኤል

የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ልታንጽ አይገባም ተብሎ በነቢዩ ሲነገረው

በቤተ እግዚእብሔር ሲጸልይ

በመዝሙረ ዳዊት ላይ ደግሞ መዝ 50 ላይ ያለውን ጥቅስ ተይዞ ተጸጽቶ እየሰገደ ሲጸልይ

በዮርዳኖስ ባሕር አጠገብ እየሰገደ ሲጸልይ

በአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ገድል ላይ ነፍሳቸውን በበገና መዝሙር እያረጋጋ ተሥሏል።

ከላይ የተጠቀሱት እንደምሳሌ ከብዙ በጥቂቱ ቅዱስ ዳዊት በሥዕል የተገለጠባቸው ጭብጦች ናቸው።

ከቅዱስ ዳዊት እና ከወላዲተ አምላክ በረከት ረድኤት ፈጣሪያችን ይክፈለን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

የካቲት 4 በዓሏ የሚታሰብላት ከጕንጪ ደም የሚፈስሳት ተአምር አድራጊዋ የእመቤታችን ሥዕል እጅግ አስደናቂ ታሪክ

(መነበብ የሚገባው)

በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

የዚኽች አስደናቂ ሥዕልን ድንቅ ታሪክ ከመጻፌ በፊት ለወንጌል አገልግሎት ወደ ኖርዌ በኼድኑ ጊዜ ከጕንጮቿ ላይ ደም የሚፈስሳት ሁላችንም የምናውቃት የእመቤታችንን የታተመች ሥዕሏን በአንድ ወንድም ቤት ውስጥ በክብር ባማረ መልኩ ተቀምጣ አይቼ በመደነቅ፤ ሥዕሏን ከየት እንደገዛት ጠየቅኹት፤ ርሱም በኖርዌ የዕቃ መሸጫ አጠገብ ወድቃ አግኝቶት ቶሎ ብሎ በገንዘቡ ገዝቷት፤ ቤቱ ወስዶ መብራት አብርቶ፤ ሸቱ ረጭቶ በክብር ባስቀመጣት ጊዜ ሌሊቱን ኹሉ እጅግ ዕጹብ ድንቅ የሚያሰኝ የዕጣን ሽታ ሲሸተውና የማዕጠንትና የምስጋና ድምፅ ሲሰማ እንዳደረ በነገረኝ ጊዜ፤ ልዑል እግዚአብሔርን በማመስገንና የተቀደሰ ሥዕሏን በመሳለም፤ የሥዕሏን ታሪክ ነገርኩት። ልጁ የገዛት ሥዕል ግን ዋናዋ የጥንቷ ናት ማለቴ ሳይኾን ያው አኹን የምንጠቀምባት ፖስት ያደረግኳት ዓይነት በዚያች በዋናዋ አምሳል የታተመችውንና የምትሸጠውን ሥዕል እንደኾነች ለማስታወቅ እፈልጋለኁ፤ ይኽን በጥንት ጊዜ የነበራትን የተቀደሰ ታሪክ ለኹሉም መጻፍ እንዳለብኝ ለራሴ ቃል ገብቼ ነበርና እነሆ ጊዜው ገጥሞልኝ በየካቲት 4 በመላው ዓለም በዓሏ የሚታሰብላትን ታሪኳን በበዓሏ ዕለት እነሆ ብያለኁ።

ስለዚኽች ድንቅ ተአምር አባ ጽጌ ድንግል አስቀድሞ በማሕሌተ ጽጌ ላይ እንዲኽ ብሏት ነበር፦

“ሥዕልኪ ማርያም ጸገየት ሥጋዌ
ከመ ዕፀ ገነት ትጸጊ ጽጌያተ ለሥርጋዌ
ሣሕለ ተአምርኪ እኩን ለትውልደ ትውልድ ዜናዌ
ቅብዕኒ ሐፈ ሥዕልኪ ወፈውስኒ እምደዌ
እስመ በኀምዙ አቍሰለኒ አርዌ”

(የገነት ዛፍ አበቦችን ለሽልማት እንደምታብብ ማርያም ሥዕልሽ ግዘፍን አበበች (ሥጋን የለበሰች መስላ ታየች)፤ የተአምርሽን ዜና ለልጅ ልጅ የምነግር እኾን ዘንድ የሥዕልሽን ወዝ ቀቢኝ፤ ከበሽታም አድኚኝ፤ አባብ አውሬ በመርዙ በኀጢአት አቍሰሎኛልና) በማለት ተማፅኗታል።

ይኸውም ከ829-842 ዓ.ም. በቤዛንታይን የነገሠው ንጉሥ ቴዎፍሎስ በቅዱሳት ሥዕላት ላይ በክፋት ተነሳሥቶ ዐዋጅ በማወጁ ወታደሮቹ በርሱ ትእዛዝ በእያንዳንዱ ቤት እየዞሩ ቅዱሳት ሥዕላትን ለማጥፋት ፍተሻ ያደርጉ ነበር፤ በኒቅያ

ከተማ አቅራቢያ አንዲት የተቀደሰች ሴት ነበረች፤ ቅዱስ ሉቃስ የሣላት የአምላክ እናት የቅድስት ድንግል ማርያም ውብ ሥዕሏን በቤቷ ውስጥ ደብቃ በማኖር በሥዕሏ ፊት መብራትን እያበራች ከልጇ እንድታማልዳት ትማፀን ነበር። የከሓዲው ንጉሥ ወታደሮቹም የአምላክ እናት ሥዕል በቤቷ እንዳለች በማወቃቸው ወደ ቤቷ በድንገት ዘልቀው ገቡ፤ ከመካላቸውም አንዱ ወታደር የእመቤታችንን ሥዕሏን በያዘው ጦር ጉንጯ ላይ ወጋት። ኾኖም ግን በእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ይኽ ክፉ ሥራው በተአምር ተተክቶ፤ ከተወጋው ከአምላክ እናት ፊት ላይ ደም ይፈስስ ጀመር።

ይኽን ግሩምና ድንቅ ተአምር ባዩ ጊዜ ወታደሮቹ ደንግጠው ሸሽተዋል፤ ሴቲቱም ይኽነን ድንቅ ተአምር ባየች ጊዜ ሌሊቱን ሙሉ በሥዕሏ ፊት መብራትን አብርታ በአምላክ እናት በቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ፊት ስትጸልይ ዐደረች፤ በነጋታውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ከጉንጯቿ ደም የፈሰሳትን የአምላክ እናት ሥዕሏን በባሕሩ ላይ እንድታስቀምጥ ታዘዘችና አስቀመጠቻት፤ ሥዕሏም በባሕሩ ላይ በመንሳፈፍ በማዕበሉ እየተነዳች ያለምንም መስጠምና መርጠብ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ጉዞዋን አድርጋ ወደ አቶስ ደረሰች። ጊዜያቶች ካለፉ በኋላ ከዕለታት በአንዳቸው ምሽት በአቶስ ተራራ የአይቬሮን ገዳም መነኮሳት የብርሃን ምሰሶ በባሕሩ ላይ ተተክሎ እንደ ፀሓይ ሲያበራ ተመለከቱ። ይኽም ተአምር ለተካታታይ ቀናቶች በመቀጠላቸው በዚያ የተቀደሰ ተራራ በምናኔ ያሉ አባቶች ኹሉ በአንድ ላይ ተሰባስበው በማድነቅ የብርሃን ምሰሶ ወደተተከለበት የአምላክ እናት ሥዕል በላዩ ላይ ወደ ተንሳፈፈበት ወደ ባሕሩ በመውረድ ወደ ሥዕሏ ለመጠጋት ቢሞክሩም ሥዕሏ ወደ ኋላዋ እየተመለሰች ሊያነሷት አልተቻላቸውም።

በዚያው የአይቮሪዮን ገዳም ረድእ (የጉልበት አገልጋይ) ኾኖ የሚኖር አባ ገብርኤል የተባለው መነኩሴ ብቻ ሥዕሏን ከባሕር ውስጥ ማንሣት የሚችል እንደኾነ የአምላክ እናት ለመነኮሳቱ ገለጠችላቸው፤ በተመሳሳይም ለአባ ገብርኤል እመቤታችን ተገልጣለት “ወደ ባሕሩ ኺድ፤ ማዕበሉንም ሳትፈራ በባሕሩ ውስጥ በእምነት ተጓዝ፤ እናም ኹሉም ለዚኽ አንተ ላለኽበት ገዳም ያለችን ፍቅርና ርኅራኄ ምስክር እንዲኾኑ፤ ሥዕሌን ከባሕር አውጣ” በማለት ነገረችው። ከዚያም በአቶስ ተራራ ያሉት መናንያን ኹሉ አባ ገብርኤልን ይዘው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፣ እያመሰገኑ፤ በማዕጠንታቸው ዕጣን እያጠኑ የብርሃን ምሰሶ ወደተተከለበት የአምላክ እናት ሥዕል ወዳለበት ወደ ባሕሩ ኼዱ፤ አባ ገብርኤልም በደረቅ መሬት እንደሚጓዝ ያለምንም ፍርሃት ወደ ባሕሩ ውስጥ በመግባት በናፍቆት ኾኖ የአምላክ እናት የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥዕሏን በደረቱ ታቅፎ ተሳለማትና ወደ ባሕር ዳርቻ ይዟት ወጣ፤ እነርሱም በደስታ ኾነው እጅ ነሷት።

ከዚያም ማግሰኞ በጠዋቱ ሥዕሏ ባረፈበት ቦታ ላይ በሚያመሰግኑበት ጊዜ ቀዝቃዛና ጣፋጭ ውሃ ከምድር ላይ ፈለቀላቸው። ከዚያም የእመቤታችንን ሥዕሏን በታላቅ ክብር በምስጋና ይዘው በመኼድ ወደ ቤተ መቅደስ አግብተው በመንበሩ ላይ አስቀመጧት።

ነገር ግን በነጋታው መነኮሳቱ ወደ ቤተ መቅደስ ገብተው መብራት ሲያበሩ የእመቤታችን ሥዕሏን ባስቀመጡበት ቦታ አላገኟትም፤ ይልቁኑ በመግቢያው በር ባለው ግድግዳ ላይ ተሰቅላ አገኟት፤ እነርሱም መልሰው በቦታዋ ላይ ቢያኖሯትም ተመልሳ በገዳሙ መግቢያ ላይ ተሰቅላ ያገኟት ነበር፤ ከዚያም እመቤታችን ለአባ ገብርኤል ተገልጻለት "ለወንድሞች እንዲኽ ብለኽ ንገራቸው፤ ከዚኽ በኋላ ሥዕሌን ማግባት የለባቸውም፤ የእኔስ ፈቃድ በእናንተ ልጠበቅ ሳይኾን እኔን በምልጃዬ ጥላ በዚኽም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም ልጋርዳችኁ እንጂ፤ ሥዕሌን በገዳሙ በምታዩበት ጊዜ ኹሉ የልጄ ምሕረትና ጸጋ ከእናንተ አይቋረጥም" አለችው።

መነኮሳቱም ይኽነን ሰምተው በእጅጉ በመደሰት ለአምላክ እናት ለእመቤታችን ክብር በገዳሙ በር አጠገብ አነስ ያለች ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ገባሪተ ተአምራት ወመንክራት (ድንቅ ተአምር አድራጊዋን) የአምላክ እናት የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥዕሏን ወደ ውስጥ አገቧት፤ የተቀደሰች የሥዕሏ መጠሪያም "የአይቬሮኗ የአምላክ እናት" ስትባል በግሪክ "ፓርታኢቲሳ" ትባላለች፤ ከዚያም በአይቬሮን ገዳም ያለችው የእመቤታችን ሥዕል ድንቅ ተአምር በዓለም ኹሉ ላይ ከተሰማ በኋላ በረከቷን ለማግኘት ክርስቲያኖች ወደዚያች ገዳም መኼድን ዝመሩ፤ ይኽ የተቀደሰ ሥዕሏና ታሪኳም ኢትዮጵያን ጨምሮ በዓለሙ ኹሉ ላይ ተሰማ፤ ዛሬም ምእመናን ይማፀኑበታል። እኔ መጋቤ ሐዲስ ሮዳስም ይኽነን የተቀደሰ ታሪኳን ዛሬ የካቲት 4/ 2008 ዓ.ም በበዓሏ ዕለት በመጻፌ እጅግ ደስታ እየተሰማኝ፤ ለአባ ገብርኤል የተለመነች እና በረከቷን እንዳሳደረችበት ዛሬም የምልጃዋ ጥላ በዚኽም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም እንዳይለየኝ በመማፀን አባ ጽጌ ድንግል ስለዚኽች ሥዕል በማሕሌተ ጽጌ ላይ ባመሰገናት ምስጋና ጽሑፉን አበቃለኁ።

"ቦ አመ ትትረከብ ምስለ ቃለ ነገር ጥዑም
ወቦ አመ ትትረአይ በለቢሰ አባል ልምሉም
ሥዕልኪ ማርያም ጽጌ ተአምር አዳም
ወአመ ዘበጣ በሰይፍ አይሁዳዊ ርጉም
እምኔሃ አንጸፍጸፈ ደም"

(ሥዕልሽ ቃልን ደስ ከሚያሰኝ ነገር ጋራ የምትገኝበት ጊዜ አለ፤ የለመለመ አካልንም ለብሳ የምትታይበት ጊዜ አለ፤ ማርያም ሥዕልሽ የተአምር አበባ ናት፤ ርጉም አይሁዳዊ በሰይፍ በመታት ጊዜ ከርሷ ሥዕል ደም ተንጠባጠበ) ይላል።

የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ በምልጃሽ እና

በቃል ኪዳንሽ የማይጠገበው በረከትሽን ዕጽፍ ድርብ አድርገሽ አሳድርቢን፤ እስቲ እናንተም በተቻላችኁ መጠን በተሰማችኁ ልክ አመስግኗት፦

ከመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ —

ብዙዎች እናንተ የምትሰግድት ፈረንጅ ለሳለው ስእል ነው አምላክ ነጭ ይሁን ጥቁር ያየው የለም የሚሉ አሉና ይሄን ለማወቅ ፈልጌ ነው ::

ይህ ጥያቄ የ1 ሰብቻ አይደለም ብዙዎቻችን በውስጣችን የሚመላለስ ጥያቄ ነው እና እግዚአብሔር ለሁሉም መልስ አለው !

ለመጀመሪያ ጊዜ የጌታን ሥዕል የሳለው ዮሐንስ ወንጌላዊ ነው ከ14-37ዓ)ም ሮምን ገዚ ጢባርዮስ ልጁ ሞቶበት አስከሬኑን ከጌታ መቃብር ላይ አኖሩት ልጁም ተነሳ በዚሕ መክንያት ዮሐንስ ለጢባርዮስ በዕለተ ዓርብ በመስቀሉ ላይ እዳየው አድርጎ ገለሜዳ አስታጥቆ ጌታን ስሎታል ድምጽም ከሥዕሉ እንደወጣ ታሪክ ይናከራል ምንጭ አምደሃይማኖት

ሌላው ሥዕል በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለሙሴ ሥዕለኪሩብን እነዲአዘጋጅ ነገረው በታቦቱ አጠገብ እንዲአስቀምጥ አዞታል ዘጸ25÷21-22 ዘኁ7÷8-9 ዘጸ21÷1 በዚሕ አይነት ለሙሴ የተሰጠው ሥዕል መነሻና መሠረት ሆኖ ለሥርአተ አምልኮ መፈጸሚያ ሆኖአል ሌላው ነጉሥ ሰሎሞን ቤተመቅደሱን በሰራ ጊዜ ይሕን መነሻ አድርጎ የ2 ኪሩብን ሥዕሎች በቅድስተ ቅዱሣኑ ወስጥ አስቀምጦአል 2ኛዜና 7÷11-12 እስራኤል የባቡን ሥዕል በዕምነት ባዩጊዜ ድነዋል ዘኁ21÷8-9 ሥዕል በአዲስ ኪዳን ለአዲስኪዳን ሥዕል መሠረቱ የብሉይ ኪዳን ሥዕል ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለሥጋዌው ሥዕለ ኪሩብ ባለበት ቤተመቅደስ አልተለየም ነበር በአርባ ቀኑ ድንግል ማርያም ወደቤተ መቅደስ ወስዳዋለች ሉቃ 2÷22-24 2÷41 ዕለት ዕለትም ሥዕለኪሩብ ካለበት ቤተመቅደስ እየተገኘ ያስተምር ነበርማቴ 21÷14 ዮሐ18 20 ሥዕል በቤተመቅደስ ባያስፈልግ ኖሮ ሥዕሉንም ከቤተመቅደስ ባወጣ ነበር ጥንቱንም እነሙሴ ሥዕል እንዲስሉ አያዝም ነበር ሐዋርያት ይሕንን መሠረት አድርገው ሥዕል ባለበት ቤተመቅደስ እየተገኙ ጸልየዋል ሉቃ 24÷51 ባጭሩ አንድ ነገር ልናገር የሙሴ በትር ታምራትን አድርጋለች ዘጸ4 -12 የየልያስ መጎናጸፊያ ወንዝ ለሁለት ከፍላለች 2ኛ ነገ2÷8የጳውሎስ ልብስ ጨርቅ ቢሆንም በሽተኛ ይፈውስ ነበር የጴጥሮስ ጥላአጋንንትን ያስወጣ ነበር

የሐዋ 5÷15 ነበር ታዲያ የጌታ ሥዕል ሙት ቢአስነሳ የጌታ መስቀል አጋንንት ቢስወጣ ምን ይደንቃል የእመቤታችን ሥዕልም እንዲሁ ቢፈውስ ማድነቅ ነው እንጅ መተቸት ምን አስፈለገ ከብዙ በጥቂቱ ይሕን ይመስላል መልካም ቀን ይሁንላችሁ።

እናት ሙላቱ ስለ ድንግል ማርያም ዝም አልልም!

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ለዘላለም ትኑር ።

በስመአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አንድ አምላክ... አሜን...

ቅዱሳት ሥዕላት

ሥዕል እግዚአብሔር ጋር የተያያዘና በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን የሚሰራበት ነው

ሥዕል በእግዚአብሔር ፊት የተሰጠ ህግ ነው ይኽውም ለሙሴ በታቦተ ሕጉ በፅላት ኪዳኑ ላይ ሥዕለ ኪሩብን እንዲስል ታዘ ነበር

በብሉይ ኪዳን የመጀመሪያው ሰአሊ ሙሴ ነው ሰለሞንም የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ በሰራ ጊዜ ሥዕለ ኪሩቤልን ስሏል።

ዘጸ25:19 ከስሪየት መክደኛው ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን አድርገህ በአንድ ላይ ትሰራዋለህ

ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ይዘረጋሉ የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ ፊታቸውም እርስ በርሱ ይተያያል የኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ ስርየትመክደኛው ይመለከታሉ።

ዘጸ37:7 ሁለት ኪሩቤልንም ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሠራ በስርየት መክደኛውም ላይ በሁለት ወገን አደረጋቸው

ከስርየት መክደኛውም ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን ሁለተኛውንም ኪሩብ በሌላ ወገን አድርጎ በአንድ ላይ ሰራቸው።

ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ የዘረጉ ሆኑ የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ሸፈኑ እርስ በራሳቸውም ተያዩ የኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ መክደኛ ተመለከቱ።

1ኛ ነገስት6:23-28በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ ቁመታቸው አስር ክንድ የሆነ ከውይራ እንጨት ሁለት ኪሩቤል ሠራ።

የኪሩብም አንደኛው ክንፍ አምስት ክንድ የኪሩብም ሁለተኛው ክንፍ አምስት ክንድ ነበር ከአንደኛው። ክንፍ ጫፍ ጀምሮ እስከ ሁለተኛው ክንፍ ጫፍ አስር ክንድ ነበረ።

ሁለተኛውም ኪሩብ አስር ክንድ ነበር ሁለቱም ኪሩቤል አንድ ልክና አንድ መልክ ነበረ የአንዱ ኪሩብ ቁመት አስር ክንድ

ነበር።

ኪሩቤልንም በውስጠኛው ቤት አኖራቸው የኪሩቤልም ክንፎቻቸው ተዘርግተው ነበር የአንዱ ኪሩብ ክንፍ አንድ ግንብ ይነካ ነበር የሁለተኛውም ኪሩብ ክንፍ ሁለተኛውን ግንብ ይነካ ነበር የሁለቱም ክንፎች በቤቱ መካከል እርስ በራሳቸው ይነካኩ ነበር ኪሩቤልንም በወርቅ ለበጣቸው።

1ኛ ነገስት6:29 በቤቱም ግንብ ሁሉ ዙሪያ በውስጥና በውጭ የኪሩቤልና የዘንባባ ዛፍ የፈነዳም አበባ ምስል ቀረጸ።

1ዜና3:5 ታላቁንም ቤት በጥድ እንጨት ከደነው በጥሩም ወርቅ ለበጠው የዘንባባና የሰንሰለት አምሳል ቀረጸበት።

ሕዝ4:1 አንተም የሰው ልጅ ሆይ ጡብን ወስደህ በፊትህ አኑራት የኢየሩሳሌምንም ከተማ ስዕል ሳልባት ክበባት።

ምሳ17;3 እማቱም ልጄ ሆይ እግዚአብሔር ይባርክህ አለችው።

አንዱን ሺህ አንዱን መቶ ብርም። መለቅሰላግር እናቱም።

ይህን ብር የተቀረጸ ምስልና ቀልጦ የተሰራ ምስል አድርጌ ከእጄ ስለ ልጄ ለእግዚአብሔር እቀድሰዋለሁ አሁንም ለአንተ እመልሰዋለሁ አለች።

ለእናቱም ገንዘቡን በመለሰላት ጊዜ እናቱ ሁለቱን መቶ ብር ወስዳ ለአንጥረኛ ሰጠችው...እርሱም የተቀረጸ ምስልና ቀልጦ የተሰራ ምስል አደረገው።

ያም የሚካ ቤት ነበረ ሰውየውም ሚካ የአምላክ ቤት ነበረው ኤፋድና ተራፊም አደረገ ከልጆቹ አንዱም ቀደሰው ካህንም ሆነለት።

ወስበሐት ለእግዚአብሔር

ምንጭ...ዓምደ ሃይማኖት

ክብረ ቅዱሳት ሥዕላት

እንደሚታወቀው ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር በእግዚአብሔርነቱ የማይታይና የማይዳሰስ ረቂቅ መንፈስ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም (የሚያመልኩትም) በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል» ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት ዐቢይ ማስረጃ ነው (ዮሐ. 4፤24)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የጌታችንን ትምህርት ተከትሎ እግዚአብሔር መንፈስ (ረቂቅ) መሆኑን ሲናገር፤ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ» ብሎአል (2 ቆሮ.3፤ 17)።

በዚሁ መሠረት የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑት ቅዱሳን መላእክትም ረቂቃን መናፍስትም መሆናቸው የታወቀ ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስም ይህንን ያረጋግጥልናል (መዝ. 103 (104)፤4)።

<u>ጥያቄ፤ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ረቂቅ መንፈስ ከሆነ፤ አገልጋዮች ቅዱሳን መላእክትም ረቂቃን መናፍስትም ከሆኑ፤ እግዚአብሔርንም ሆነ መላእክትን በሥዕል መግለጽ ይገባልን? እግዚአብሔር ይህንን ይመስላል፣ መላእክቱም ይህን ይመስላሉ እያሉ እነሱን በስዕል እየሳሉ መግለጽ ተገቢ ነውን?</u>

መልስ፤ እግዚአብሔር በባሕርዩ (በመለኮቱ) በስዕል ወይም በቅርጽ መግለጽ ፈጽሞ አይገባም፤ ወይም ሰማይና ምድርን የመላውን እግዚአብሔርን በመተው ስዕል እየሳሉ፤ ቅርጽ እየቀረጹ አማልክትን (ጣዖታትን) ማምለክ ዐቢይ ኃጢአት መሆኑን ራሱ እግዚአብሔር ለሙሴ አዞታል እንዲህ ብሎ፤ «ከግብጽ ከባርነት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁንልህ፤ በላይ በሰማይ ካለው ፤ በታችም በምድር ካለው ነገር የማናቸውም ምሳሌ፣ የተቀረጸውንም ምስል ለእንተ አታድርግ፤ አትሰገድላቸውም፤ አታምልካቸውም፤ በሚጠሉኝ እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምህረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ» (ዘጸአ. 20፤1-6)።

ነገር ግን እግዚአብሔር ለወዳጁ ለአብርሃም በሦስትነቱ ምስጢር ሦስት መንገደኞችን መስሎ እንደተገለጠለት መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ዘፍጥ. 18፤ 1-15)። ስለዚህ ይህንን ታሪክ በሥዕል መግለጽ የሚገባ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን «የአብርሃም ሥላሴ» በሚል ርእስ በሥዕል እየገለጸች ስታስተምርበት ትገኛለች።

ቅዱሳትን መላእክትም በአምሳለ ሰብእ ማለት በሰው አርአያ ለአስማኤል እናት ለአጋር (ዘፍጥ. 16፤7) ለያዕቆብም (ዘፍጥ. 32፤1) ለበለዓምም (ዘኁል. 22፤31) ለኢያሱም (ኢያሱ 5፤13)፤ ሰውን መስለው ስለተገለጹላቸው የእነሱን መገለጽ፣ ተራዳኢነታቸውንና ታዳጊነታቸውን ለምእመናን ለመግለጽ ታሪኩን በሥዕል ማቅረብ የሚገባ ነው። በመሆኑም በኦሪት ዘጸአት በምዕራፍ ሃያ ከተጻፈው ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ጋር የሚቃረን አይደለም። በሰው አምሳል በመግለና ለእነሱም የጸጋ (የአክብሮት) ስግደት ማቅረብ ነቢዩን ኢያሱን መምሰል ነውና የሚገባ ነው (ኢያሱ 5፤ 13)።

ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ሦስቱን ወጣቶች ከተወረወሩበት የእሳት ጉድጓድ ያዳናቸውን ቅዱስ ገብርኤልን በሥዕል ሥሎ ማቅረብ የእምነት ሥራ እንጂ የኃጢአት ሥራ አይደለም (ዳን. 3፤ 1-30)። ወደ እሳት የተጣሉትንም ምእመናን ከእግዚአብሔር ተልኮ ላዳነ ለእግዚአብሔር መልአክ ሥዕል የአክብሮት ስግደት ማቅረብ ሥርዓተ ሃይማኖትን መፈጸም ነው እንጂ መናፍቃኑ እንደሚተቹት ጣዖት ማምለክ አይደለም። ንጉሡ ናቡከደነጾርም መልካም ነገር ለሠራለት ለነቢዩ ዳንኤል ተደፍቶ የጸጋ ስግደት እንዳቀረበለትና ይህንንም በማድረግ እንዳልተወቀሰ፤ እውነተኞቹ ምእመናንም በተራዳኢውና በአማላጁ በቅዱስ ገብርኤል ሥዕል ፊት ተደፍተው የአክብሮት ስግደት ቢያቀርቡለት የእግዚአብሔር ወገኖችና የቅዱስ ገብርኤል ወዳጆች ያሰኛቸዋል እንጂ አያስወቅሳቸውም (ዳን. 2፤ 46)።

ሥዕልን ዕጣን የአምልኮት መግለጫዎች እየሆኑ እንደሚቀርቡ የታወቀ ነገር ነው። ለምሳሌ ሥዕል በሐገ ወጥ ተጠቃሚዎች የጣዖት መግለጫ እየሆነ ይቀርብ እንደ ነበር ከነቢዩ ሕዝቅኤል እንረዳለን። (ሕዝ. 8፤ 7-13)።

ስለሆነም በነቢዩ አገላለጽ ኃጢአትና በደል ሆኖ የተቆጠረው ሥዕሉ ሳይሆን በሥዕሉ አማካይነት አምልኮ ጣዖት መፈጸሙ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር መራዊት የሆኑትን ቅዱሳን መላእክትን በሥዕልም ሆነ በቅርፅ አዘጋጅቶ ማቅረብ መፈቀዱን ከኦሪቱና ከመጽሐፈ ነገሥት መረዳት እንችላለን። ነቢዩ ሙሴና ንጉሡ ሰሎሞን የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑትን ኪሩቤልን በወርቅ አዘጋጅተው በታቦቱ መክደኛ ላይ እንዲያስቀምጡ እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል (ዘጸአ. 25፤ 18 ፣ መጽ. ነገ. 8፤7)።

ስለዚህ ጨረቃ በከዋክብት ታጅባ ስትታይ እጅግ እንደምትደምቅ፤ ተራራም በዝናብ ወራት በአበባ ተሸፍኖና ደምቆ ሲታይ እንደሚያምር ቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔር አገልጋዮች በሆኑት በቅዱሳን መላእክት፤ በጻድቃንና በሰማዕታት ሥዕሎች አሸብርቃና ደምቃ ስትታይ በእርግጥ የእግዚአብሔር መንበር (ዙፋን) ያለባት የእግዚአብሔር ቤት መሆንዋን በበለጠ መረዳት እንችላለን።

ከሥዕል የሚገኙ ዐበይት ጥቅሞች

የጥንቱና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የሚከተል ክርስቲያን ሁሉ ከቅዱሳት ሥዕሎች ሁለት ዐበይት ጥቅሞችን ያገኛል። ይኸውም ትምህርትና ረድኤት ናቸው።

ትምህርት በሥዕሎች አማካይነት የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በምሕጻረ ቃል በጉላና በተረዳ ሁኔታ ማጥናትና ማወቅ ይቻላል። በኦሪት ዘፍጥረት በሁለተኛውና በሦስተኛው ምእራፍ የተገለጸው የአዳምና የሔዋን አፈጣጠር በእባብና (በሰይጣን) አሳችነት በኃጢአት መውደቅ በሥዕል ሲገለጽ የበለጠ መረዳት ይቻላል። በዚሁ ዓይነት አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ለእግዚአብሔር ሊሰዋው ሲዘጋጅና እግዚአብሔርም በይስሐቅ ፈንታ በጉን እንዳቀረበለት በሥዕል ሲገለጽ ታሪኩ የበለጠ ግልጽ ይሆናል (ዘፍ. 22፤1-14)።

ይልቁንም ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የነበረው ቃለ እግዚአብሔር (አካላዊ ቃል) በኋለኛው ዘመን ሰውን ለማዳን ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ ከሥጋዋ ሥጋን ፣ ከነፍስዋ ነፍስን ነስቶ ከኃጢአት ብቻ በቀር ፍጹም ሰው ሆኖ በድንግልና የተወለደውና ተሰቅሎ በሞቱ ዓለሙን ማዳኑን በሥዕል ገልጾ ማቅረብ መስበክ፤ ማስተማር ነው። በዚህም መሠረት የጌታችንን የልደቱን ታሪክ፣ የጥምቀቱን ታሪክ፣ የስቅለቱን ታሪክ፣ የትንሣኤውንና የዕርገቱን ታሪክ በሥዕል ነድፎ ለምእመናን ማቅረብ ማለት የጌታችንን ወንጌል መንግሥት መስበክና ማስተማር ማለት ነው።ምክንያቱም ሥዕል ራሱ በጉልህ የተጻፈ ጽሑፍ ማለት ነውና። ጌታችን ተወለደ፣ ተጠመቀ፣ ተሰቀለ ፣ ሞተ፣ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ... የሚለው የወንጌሉ ታሪክ በሥዕል ማቅረብ ማለት ታሪኩን በጉልህ ጽፎ ማቅረብ ማለት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስገላትያ ክርስቲያኖች ተሳሳተ ሲጽፍ «የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፤ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር» ያለው ኢየሱስና ታሪኩን በሚገባ አውቀውትና ከልብም ተረድተውት እንደ ነበር ስመግለጽ ነው (ገላ.3፤ 1-2)።

ስለዚህ ከላይ እንደተገለጸው ቅዱሳት ሥዕሎች በመመልከትና ልብ ብሎ በማንበብ (በማስተዋል) ታሪኩን በሚገባ ማወቅና መረዳት ስለሚቻል ፤ ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ሥዕሎች የክርስትና ሃይማኖት አስተማሪዎችና አስረጂዎች መሆናቸውን መገንዘብ ተገቢ ነው።

ሁለተኛው ጥቅም ከቅዱሳት ሥዕሎች የሚገኘው ሌላው ዐቢይ ጥቅም ደግሞ ረድኤት (ርዳታ) ነው። በሕይወተ ሥጋ ያለ ማንኛውም ሰው ይኑሩም ይሙቱም የዘመዶቹን ፎቶግራፍ በቤቱ፤ በመኝታ ቤቱ ወይም በቢሮው ይሰቅላል፤ ወደ ተሰቀለውም ፎቶግራፍ በየጊዜው ያተኩራል፤ ይኸውም አንደኛ ፍቅሩን ስመግለጽ፣ ሁለተኛ ስማሰብና ስማስታወስ ነው። በዚሁ መሠረት በሥርዓተ ሃይማኖትም ምእመናን የክርስቶስን፣ የቅድስት ድንግልን፣ የመላእክትን፣ የጻድቃንን የሰማዕታትን ሥዕሎች በቤተ ክርስቲያን፣ በቤታቸው፣ በጸሎት ቤታቸው፣ በጸሎት መጻሕፍቶቻቸው የሚያደርጉት፤ አንደኛ ፍቅራቸውን ስመግለጽ፣ ሁለተኛ ስማሰብና ስማስታወስ፣ ሦስተኛ ከሥዕሎቹ ባለቤቶች ርዳታን፣ አገዛን ፣ ምልጃንና በረከትን ስመቀበል ነው።

ለምሳሌ- በጌታችን ሥዕል ፊት ቆሞ መጸለይ ከጌታ ምሕረትንና ይቅርታን ለመቀበል ነው። ጌታችን በ መስቀሉም ሆነ በሥዕሉ አማካይነት ይቅርታን ምሕረትን ይሰጣል። እንደሚሰጥም በዚሁ የተጠቀሙትን ምእመናን ጠይቆ መረዳት ይቻላል። በቅድስት ድንግልን፣ በቅዱሳን ሥዕሎች ፊት ቆሞ በመጸለይም የሥዕሎቹ ባለቤት ከሆኑት ርዳታን፣ እገዛን፣ በረከትን ለማግኘት ነው። ስዚሁም ምስክሮቹ በጌታና በቅ ድስት ድንግል ሥዕሎች፣ በቅዱሳን መላእክትና በቅዱሳን ሰማዕታት፣ በጻድቃን ሥዕሎች እየተማጸኑ ከ ፍተኛ ርዳታንና በረከትን የተቀበሉትን ካህናትና ምእመናን ጠይቆ መረዳት ይገባል። ነገር ግን ዝም ብ ሎ መንቀፉ ጉዳትን እንጂ ጥቅምን የማይሰጥ መሆኑን መረዳት ይገባል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለነበረበት በጣም ቅርብ የነበሩት የጥንት ክርስቲያኖች በጌታችን ሥዕል፣ በቅድስት ድንግል ሥዕልና በቅዱሳን ሥዕሎች ይማፀኑ እንደ ነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይመሰክራል። በዘመና ችን ተቆፍረው የተገኙ የጥንት አብያተ ክርስቲያናት ፍርስራሾችም በሥዕላተ ቅዱሳን መማፀን ጥንታዊ ትውፊት (ሥርዓት) እንደሆነ ያመለክታሉ።

ታሪክን መካድ ደግሞ አያትና ቅድመ አያትን መካድ ማለት ነው። ስለ ሥዕል ክብር የቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ ታሪክ ምስክር ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው በታሪክ መንገድ መሆኑ የታወቀ ነው። በዚሁ መሠረት የታወቀው ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘቂሳርያ ስለ ጌታ ሥዕል እጅግመርና አመጣጥ ጽፎ ያቀረበውን ብፁእ አባ ጎርጎርዮስ ሊቀ ጳጳስ ዘሸዋ በመጽሐፋቸው ጠቅሰውታል። እኛም የጥቅሱን ፍሬ ነገር ቀጥለን ጠቅሰነዋል።

«ንጉሥ ዐብጋር በዑር (ኤዴሣ) ከተማ የአገሩ ንጉሥ በመሆን ጌታችን በነበረበት ዘመን ይኖር ነበረ፤ ስ ሙም (ልዑካን) ይባል ነበር። ዐብጋር ማለት በከለዳውያን ቋንቋ ቁማር ማለት ነው። ዐብጋር በዚያ ዘመ ን በጠና ታሞ ነበር፤ የጌታችንን ተአምራት በዝና ሰምቶ ይፈውሰው ዘንድ ደብዳቤ ጽፎ ለጌታችን ላከ ለት፤ ጌታችንም ደብዳቤውን ከመልእክተኛው እጅ ተቀብሎ ካነበበው በኋላ «ሳያየኝ ያመነኝ ዐብጋር ብፁዕ ነው» ብሎ ዐብጋርን በማመስገን በሱ ሰም እንዲፈውሰው ከደቀ መዛሙርቱ መካከል አንዱን እ ንደሚልክለት በመግለጽ መልስ ላከለት። ነገር ግን ከጌታ ጋር ተገናኝቶ የተመለሰው የዐብጋር (ዩካማ) መልእክተኛ ሠዓሊ ስለነበር ከጌታችን ጋር ሲነጋገር ፊቱን በሥዕል ነድፎ (ሥሎ) ከደብዳቤው ጋር ይዞ ተመለሰ። ከዚያም እንደ ደረሰ ከጌታ የተላከውን ደብዳቤ ለታመመው ንጉሥ አነበበለት፤ ሥዕሉንም አሳየው። በዚያን ጊዜ በሽተኛው ንጉሥ የጌታችንን ቃል ከደብዳቤው ሰምቶና ሥዕሉንም በዓይኑ ተመ ልክቶ ወዲያው ከሕመሙ እንደ ተፈወሰ ታሪኩ ያስረዳል (አባ ጎርጎርዮስ፤ የኢ. ኦ. ተ. ቤተ ክርስቲያን ታሪክ 1974 ገጽ 119- 120)።

እንደገናም ይኸው አውሳብዮስ ስለ ጌታችን ሥዕል የሰጠው ምስክርነት እንዲህ የሚል ነው «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ ደሙን እያንጠፈጠፈ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ጎልጎታ በሚጓዝበት ወቅ ት እያለቀሱ ከሚከተሉት ደጋግ ሴቶች መካከል ቬሮኒካ የተባለች ደግ ሴት የራስዋን መሸፈኛ አውልቃ ፊቱን እንዲያድፍበት (እንዲጠርግበት) ለጌታ ወረወረችለት፤ ጌታችንም በደምና በላብ የተጠመቀውን ፊ ቱን ጠርጎ ሲመልስላት ሥዕለ ገጹ ማለት የፊቱ መልክ በሻሽዋ ላይ ታትሞ ቀረ» በማለት ከላይ የጠቀ ስነው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ ይመሰክራል።

ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ደግሞ ወላዲተ አምላክ በነበረችበት ከፍለ ዘመን የነበረው ሐዋር ያው ቅዱስ ያዕቆብ የጌታን ታሪክ (ወንጌል) ሲጽፍ ስለ ወላዲተ አምላክም ብዙ ጽፎአል። በዚህ የያዕ ቆብ ወንጌል (ያዕቆብ ታሪክ) በተባለው የትውፊት መጽሐፍ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ለመጀመሪያ ጊዜ የማርያምን ሥዕል መሣሉ ተጽፎአል።

አውሳብዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘቂሳርያና ሌሎችም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እንደ መሰከሩት የጥን ትዋ ቤተ ክርስቲያን ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል ፣ ለወላዲተ አምላክ፣ ለቅዱሳን መላእክት፣ ለ ጻድቃንና ለሰማዕታት ሥዕሎች ከፍ ያለ ክብር እንዲደረግላቸውና የጸጋና የአክብሮት ስግደት እንዲቀር ብላቸው ስታስተምር ኖራለች። ምእመናንም በቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት በሚጸልዩበት ቤተ ክ ርስቲያንና በቤታቸው በሚገኘው በግል ጸሎት ቤታቸው የጌታችንን፣ የቅድስት ድንግል ማርያምና የቅዱ ሳንን ሥዕሎች በግድግዳው በመስቀልና የክብር ስግደት በማቅረብ ሲማፀኑባቸው ኖረዋል።

በዚሁ ሁኔታ የሥዕል ክብር በጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተጠበቀ እስከ ሰምንተኛው መቶ ክፍለ ዘ መን መጀመሪያ ድረስ ከቆየ በኋላ ሳይታሰብ በድንገት ከክርስቲያኖቹ መካከል ጥቂቶች ሰዎች የሥዕል ን ክብር በመቃወም ተነሡ። በዚሁ ምክንያት በርምና በቢዛንታይን ግዛቶች ከባድ ክርክርና ሁከት ተቀ ሰቀሰ። በዘህ ጊዜ በ797 ዓ.ም የምስራቅ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጉባዔ አድርገው የቅዱሳንን ሥዕሎች ማክበርና መሳም (መሳለም) እንደሚገባ ለሥዕሎቹም የአክብሮት ስግደት ማቅረብ ተገቢ መሆኑን በሰፊ ው አትተው ወሰነዋል። እንሆ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፕሮቴስታንቶች እስከ ተነሡበት እስከ አሥራ ስድስ ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ የሥዕል ክብር ከፍተኛውን ቦታ ይዞ ቆይቶአል። በአሁኑ ክፍለ ዘመንም በመላው ዓለም በሚገኙ ከሦስት መቶ ሚልዮን በላይ በሚሆኑ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖችና ከዘጠኝ መቶ ሚልዮን በሚበልጡ ካቶሊካውያን ክርስቲያኖች ዘንድ የሥዕል ክብር ከፍተኛውን ቦታ ይ ዞ ይገኛል።

እነዚህ ከአንድ ሺህ አራት መቶ ሚልዮን በላይ የሚሆኑ የዓለም ክርስቲያኖች በሙሉ በአካል ሦስት በ መለኮት (በአምላክነት) በባሕርይ አንድ አምላክ ብቻ የሆነውን እግዚአብሔርን እያመለኩ ለቅድስት ድ ንግል ፣ ለቅዱሳን መላእክት፣ ለጻድቃንና ለሰማዕታት፣ ለቅዱስ መስቀልና ለቅዱሳት ሥዕሎች የጸጋና የ አክብሮት ስግደት ያቀርባሉ፤ ለሥዕሎች ተማሳጽኖ እያቀረቡ የሥዕሎቹ ባለቤቶች ከሆኑት ከጌታችንና ከቅዱሳን ዘንድ ርዳታን፣ በረከትን እገዛን ያገኛሉ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉና በሥዕሉ አማካይነት ምሕረቱንና ቸርነቱን ይስጠን ። ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም፣ ቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃንና ለሰማዕታትም በሥዕላቸው አማከ ይነት በረከቱንና ረድኤትን ከጌታ ዘንድ እያማለዱ እንዲያሰጡን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልን «አ ሜን»።

አቡነ ገብርኤል በ1990 ካሳተሙት «ክብረ ቅዱሳን» ከሚለው መጻሕፍ የተወሰደ።



ቅዱሳት ስዕላት

ስዕል ህልውና ያለው ግዑዝም ሆነ መንፈሳዊ አካል በአእምሯችን የሚሳልበት ተፈጥሯዊ መንገድ ነው። በአይናችን የምናያቸውም ሆነ በምናባችን የምንስላቸውን ነገሮች የምንረዳቸው በአእምሯችን በተሳሉበት አይነትና ሁኔታ ነው። ይህን በአእምሯችን የተቀረጸውን ረቂቅ ስዕል ጸጋው በሰጣቸው ጥበበኞች በኩል በቀለምና በጨርቅ /ወረቀትሏተዋህዶ በግዙፍ ስዕልነት ይገለጣል። እኛ ሰዎች በተፈጥሯችን ዕለት ዕለት የምናመልከውን እግዚአብሔርን፣ የምናከብራቸው ቅዱሳንን ቀርቶ፣ በአካል ሳንተዋወቅ በድምጽ ብቻ የምናውቃቸው ሰዎች ቢኖሩ አንኳን፣ ስብዕናቸው በአእምሯችን ይቀረጻል። በአእምሯችንም የሚሳሉት በምናባችን ባላቸው ዓይነት ስዕል /Imagination/ ነው። ይህ ተፈጥሯዊ ባሕርያችን ነው። ወንጌል ክርሰቶስ ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮና እስከ ቢታንያ ተራራ የተጓዘበትን መንገድ የሚገልጥ የምስራች ነው። ይህን የክርሰቶስ ጉዞ የምንረዳው በህሊናችን ስዕል መጠን ነው። የቅዱሳንንም ገድል እንዲሁ። የስዕል መነሻው በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በገድላት የተገለጸ አንድ ድርጊት ወይም ሁኔታ ሆኖ ዓላማውም ያንን በአምሯችን እንዲሳል መርዳት ነው። በተለይ ትምህርት ለሌላቸው ምዕመናን ስዕል መጽሐፍ ቅዱስን የሚተካም ነው። ወደ ቤተክርስቲያን ስንገባም ሆነ በስዕል ፊት ለጸሎት ስንቆም፣ በስዕሉ አማካኝነት ህሊናችን ወደ ሰማይ ይነጠቃል፤ በመንፈስ በእግዚአብሔር ፊት እንቀርብበታለን። ስለዚህ ስዕል ወንጌልን የምንማርበት የተዋበ መጽሐፋችን፣ የስዕሉን ባለቤት በህሊናችን የምንስልበት መስታወታችን፣ ስርዓተ አምልኮ ለመፈጸም የምንጠቀምበት መሳሪያችን ነው።

1. መንፈሳዊ ስዕልና መጽሐፍ ቅዱስ

ከመገናኛው ድንኳን ጀምሮ በቤተ መቅደስ ያለ ስርዓትና ንዋየ ቅድሳት በሰማይ ባለው መቅደስ ያሉ ንዋየ ቅድሳት ምሳሌ /ነጸብራቅሏነው። ሙሴ "በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ"። ዘጸ.25፣40 ተብሎ እንደታዘዘና ቅዱስ ጳውሎስም "በተራራው እንደ ተገለጠልህ ምሳሌ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ ብሎት ነበርና"። ዕብ.8፣5 ብሎ እንደመሰከረው፣ ምድራዊው ቤተመቅደስ የሰማያውም ምሳሌና የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው። ስዕልን ጨምሮ እያንዳንዱ በቤተመቅደስ ያሉ ንዋየ ቅድሳት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የተገኙ አይደሉም። ይልቁንም ምንጫቸው እና ሁሉንም አንዲሆን ያዘዘው እርሱ እግዚአብሔር ነው። ንዋየ ቅድሳቱ መኖራቸው ብቻ ሳይሆን እነዚህን ንዋየ ቅድሳት ለማዘጋጀት ጥበብን የቸረውም ራሱ እግዚአብሔር ነው። በመጀመሪያ ከታቦቱ ጀምሮ በቤተ መቅደስ ያሉ ንዋየ ቅድሳት የተዘጋጁት ባስልኤል አማካኝነት ነበር። "እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው። እይ ከይሁዳ ነገድ የሚሆን የሆር የልጅ ልጅ፥ የኡሪ ልጅ ባስልኤልን በስሙ ጠርቼዋለሁ። በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም በማስተዋልም በእውቀትም የእዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት፤ የጥበብን ሥራ ያስተውል ዘንድ፥ በወርቅና በብር በናስም ይሰራ ዘንድ፥ ለፈርጥ የሚሆነውን የዕንቊ ድንጋይ ይቀርጽ ዘንድ፥ እንጨቱንም ይጠርብ ዘንድ፥ ሥራውንም ሁሉ ይሠራ ዘንድ እኔም እነሆ ከእርሱ ጋር ከዳን ነገድ የሚሆን የአሂሳሚክን ልጅ ኤልያብን ሰጠሁ፤ ያዘዝሁህን ሁሉ ያደርጉ ዘንድ በልባቸው ጥበበኞች በሆኑት ሁሉ ጥበብን አኖርሁ። የመገናኛውን ድንኳን፥ የምስክሩንም ታቦት፥ በእርሱም ላይ ያለውን የስርየት መክደኛውን፥ የድንኳኑንም ዕቃ ሁሉ፥ ገበታውንም ዕቃውንም፥ ከዕቃው ሁሉ ጋር የነጻውን መቅረዝ፥ የዕጣን መሠዊያውን፥ ለሚቃጠል መሥዋት የሚሆነውንም መሠዊያ ዕቃውንም ሁሉ፥ የመታጠቢያውን ሰንም መቀመጫውንም፥ በብልሃት የተሠራውንም ልብስ፥ በክህነት እኔን የሚያገለግሉበትን የካህኑን የአሮንን ልብሰ ተክህኖና የልጆቹን ልብስ፥ የቅብዓቱንም ዘይት፥ ለመቅደሱ የሚሆን የጣፋጭ ሽቱውንም ዕጣን እንዳዘዝሁህ ሁሉ ያድርጉ።" ዘጸ.31፣1-10

ይህ አጠቃላይ ንዋየ ቅድሳቱን በሚመለከት የተነገረ ሲሆን ስዕል በተመለከተም እንዲህ ታዟል። "ሁለት ኪሩቤል ከተቀጠቀጠ ወርቅ ሥራ፥ በስርየት መክደኛውም ላይ በሁለት ወገን ታደርጋቸዋለህ። ከስርየት መክደኛውም ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን፥ ሁለተኛውንም ኪሩብ በሌላው ወገን አድርገህ በአን ድ ላይ ትሠራዋለህ። ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ይዘረጋሉ፥ የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ፥ ፊታቸውም እርስ በርሱ ይተያያል፤ የኪሩቤልም ፊቶቻቸው ወደ ስርየት መክደኛው ይመለከታሉ"። ኦሪ.ዘጸ.25፣18-20 አንዳንዶች ይህ በምስል ስለቀረጹት ኪሩቤል እንጂ ስለ ስዕል አይገልጽም በማለት ለማጣጣል መሞከራቸው አልቀረም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን የሰለሞን ቤተመቅደስ በስዕል የተሞላ እንደነበር ያስረዳናል። "በቤቱም ግንብ ሁሉ ዙሪያ በውስጥና በውጭ የኪሩቤልና የዘንባባ ዛፍ የፈነዳም አበባ ምስል ቀረጸ"። 1ኛ ነገ.6፣23:29:36:39። ከታቦቱ ጀምሮ የቤተመቅደሱ ግድግዳ፣ አምዱ (ምሰሶው)፣ በሩ፣ የነሐሱ መቀመጫ ሁሉ የኪሩቤል (የመላእክት) ስዕል (ምስል) ነበረበት።

2. ስዕልና ጣዖት

ጣዖት ማምለክ እጅግ ጸያፍ ኃጢያት ነው። ከ10ቱ ትዕዛዛት ሁለተኛው፣ ‹‹ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፡ አትስገድላቸው። ዘፀ 20:3-5፤ ዘዳ.5፣8። የሚል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው ይህንንም የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም በማለት ገልጾልናል። 1ቆሮ. 6:9,10:: ጣዖት ማምለክ እግዚአብሔርን በመካድ የሚጀመር፣ በዓላማ የሚፈጸምና ከእርሱ ውጪ ለሌሎች አማልክት መገዛትና ነው። ነገር ግን ጣዖት የሚለው ቃል ለቅዱሳት ስዕላት የሚመጥን አይደለም። በፍጹም!!!

ፕሮቴስታንት ወገኖቻችን ስዕልን ጣዖት በማለት ሊያስረዱን ሲደክሙ እያየን እናዝንላቸዋልን። አንድ ክርስቲያን ራሱን ምን ያህል ቢጠራጠር ስዕልን ጣዖት ሊል ይችላል? እንዴት በሆነ እምነት፣ በምንስ ዓይነት ማስረጃና እንዴት ባለ አስተሳሰብ ስዕል ጣዖት ሊሆን ይችላል? ጥላው ጣዖት እንዳልሆነ እርግጠኛ መሆን የሚችል ማንም ስዕል ጣዖት አለመሆኑን እንዴት መረዳት ያቅተዋል? በምንስ አይነት አመክንዮ ስዕልን ጣዖት አድርጎ ማስረዳት ይቻላል? እንኳን ዛሬ አምላክን በስጋ ተገልጦ ባየንበት በሐዲስ ኪዳን ዘመን ይቅርና፣ እግዚአብሔር ማንነቱ በግልጥ በማይታወቀበት በኦሪቱ ዘመን ስዕል ጣዖት አልሆነም፣ አልተባለምም። እውነት ለመናገር ስዕልን ጣዖት ማለት የጣዖትን ትርጉም በቅጡ ካለማወቅ እና በጣም ተጠራጣሪ ከመሆን የሚመነጭ ነው። ሰው አንድ ሲደመር አንድ ሶስት ነው ብሎ ራሱን ካሳመነ፣ አንድ ሲደመር አንድ ሁለት መሆኑን እንደማስረዳት የሚከብድ ነገር የለም። ሰዕል ጣዖት ሊሆን ወይም ጣዖት ሊባል የሚችልበት ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃም የለም። ይህን ሀሳብ ይበልጥ ለመረዳት እነዚህን ተቃራኒ ነገሮች በንጽጽር እንመልከት።

የፈርያን ጠንቋዮች በትር እና የሙሴ በትር ተቃራኒ ናቸው። አንዱ በጥንቆላ (በአጋንንት) መንፈስ ሌላኛውም በእግዚአብሔር መንፈስ የሚሰሩ። ሁለቱም ግን አባብም በትርም መሆን ችለው ነበር። በጨረሻ ላይ የሙሴ እባብ የጠንቋዮቹን አባብ ዋጠቻቸው። የሙሴ በትር ከዚህ በተጨማሪ የኤርትራን ባህር ከፍሏል። ዘጸ.14፣15 በሲና በረሃ ከዓለት ላይ ውሀ አፍልቋል። ዘኅ.20፣11 ሙሴ የቃልኪዳኑን ጽላት ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ሲመጣ፣ እስራኤላውያን እያመለኩ የጠበቁት የጥጃ ምስል ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ናቸው። እስራኤላውያን ከነሐስ ቀጥቅጠው የሚያመልኩትና እባብና (2ኛ. ነገ.18፣4) ሙሴ ከነሐስ እባብ ቀጥቅጦ በአላማ የሰቀለው እባብ ተቃራኒ ነገሮች ናቸው። አንዱ ገዳይ ሲሆን ሌላኛው መድኃኒት ነበር። ዘኁ.21:8 እንዲያውም ይህ ሙሴ በዓላማ የሰቀለው እባብ በመስቀል ተሰቅሎ ላዳነን ለክርስቶስ ምሳሌ ሆኗል። ዮሐ.3:14:: እንዲህ ብዙ ተቃራኒ ንጽጽሮች ማቅረብ ይቻላል። አኒህ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች አንዱ በአጋንንት መንፈስ የሚሰራ እርኩስ (ጣዖት) ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚሰራ ቅዱስ ነው። እግዲህ ይህንን ልዩነት ወደ ጎን በመተው በጅምላ ሁሉንም ጣዖት እንደማለት ያለ ስህተት ከወዴት ይገኛል?

አባ ዮሐንስ ደማስከሰ የተባለው አባት ይህንን ተቃርኖ ሲያስረዳ እንዲህ አለ። "እግዚአብሔር አይሁድ ከነበሩበት የጣዖት አምልኮ ፍቅር የፈወሳቸው በተመሳሳይ መንገድ ነው። አንድን በሽታ በራሱ ክትባት እንዲከላከሉ እንዲሁ ከጣዖታቸው ፈወሳቸው። ስለዚህ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ንዋያት በተቃራኒው ጣዖቶቻቸውን የሚያጠፉባቸውና የተቀደሱ ናቸው። ዛሬም ንዋየ ቅድሳት ጣዖታትን የምናጠፋባቸው እና ከእግዚአብሔር ጋር መሆናችንን እርሱን ብቻ እንደምናመልክ የምናረጋግጥባቸው ናቸው። እኛ አዋቂዎች ነን፣ በአእምሮ ሕጻናት እንደሆኑት በጣዖት ተጠልፈን የምንወድቅ አይደለንም። በቅዱሳት ንዋያትም እንዴት እንድንገለገል እናውቃለን። ከራሱ ከፈጣሪያችን በተማርነው መሰረትም እንተገብራለን፣ ጣዖትና ቅዱሳት ንዋያትም የምንለይበት ጸጋም ተሰጥቶናል"።

ስለዚህም ፕሮቴስታንት ወገኖችን ጣዖትና ቅዱሳት ንዋያትን የመለየት እምነቱና ድፍረቱ ይኖራችሁ ዘንድ እንመክራለን።

3. ስዕልና የፕሮቴስታንት መንትያ አቋም


/icons and protestants double standard/

ፕሮቴስታት ወገኖች ምንም እንኳን ስዕል ጣዖት ነው ሲሉ ቢደመጡም በተቃራኒው እነርሱ ሲጠቀሙበት እንመለከታለን። በበብዙ መጽሐፍቶቻቸው፣ መጽሔቶቻቸው እና በመዝሙሮቻቸው ስዕል መጠቀሙ እየተለመደ ነው። እነርሱ ይህን እያደረጉ የእኛን ስዕል ግን ዘወትር ሲያወግዙ ይደመጣሉ። ይህ ዘወትር የምናስተውለው በአንድ ነገር ላይ ያላቸው መንትያ አቋም /double standards/ ነው። እነርሱ ለሌላ ሰው እየጸለዩ የቅዱሳንን ጸሎት እንደሚቃወሙት ዓይነት ማለት ነው። የሚገርመው ደግሞ ከሰዕል በላይ ፊልምን ሳይቀር የመቀበላቸውና የመጠቀማቸው ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ የኢየሱስ ክርስቶስን ፊልም በመተርጎምና በማሰራጨት የተሳተፈችው የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ናት። አንድ ታዋቂ የፊልም ተዋናይ የኢየሱስ ክርሰቶስን ገጸ ባሕርይ ተላብሶ የሰራውን ፊልም መቀበል ከቻልን የኢየሱስ ክርስቶስ ስዕልን እንዴት ጣዖት ልንል እንችላልን?

በርግጥ በስዕል ዙሪያ ያለው የፕሮቴስታንት እምነት በከፊል መሻሻል እየታየበት እንደሆነ አያስተዋልን ነው። ስዕልን ጣዖት አይደለም ከማለት አልፈው በመጽሐፍት ቤቶቻቸው ጭምር ስዕል መጠቀምና መሸጥ የጀመሩ አሉ። ይህ እንዴት ሆነ ብለን ስንጠይቅ አስገራሚ ምላሽ እናገኛልን። ስዕልን ለአምልኮ መጠቀም ተከለከለ እንጂ ለትምህርት መጠቀም ምንም ችግር የለውም። ምንም እንኳን ይህ የጥቂቶች ሀሳብ ቢሆንም አዚህ መረዳት ላይ የረደሱትን ሳናደንቅ አናልፍም። ነገም ከዚህ የተሻለ መረዳት ላይ እንዲደርሱ ተስፋ እናደርጋለን።

4. በስዕል ፊት ጸሎት ማድረግና መስገድ፤

ዛሬ ዛሬ ስዕልን ለትምህርት ማስተማሪያነት መጠቀም አግባብ ነው የሚሉ ፕሮቴስታንት እየበረከቱ ነው። ነገር ግን ይህ እምነታቸው በስዕል ፊት መስገድንና ጸሎት ማድረግን ወደ መቀበል ማደግ ይገባዋል። እስኪ በስዕል ፊት መጸለይና መስገድን የሚቃወሙ ፕሮቴስታንቶችን በቅንነት እንጠይቃቸው። በስዕል ፊት መጸለይ ሰህተት ከሆነ በምን ፊት መጸለይ ትክክል ይሆናል? እስኪ ንገሩን? በግድግዳ ፊት? አንዲሁ ምንም በማይታይ ጭር ባለ አየር ስፍራ? ወይስ አይንን ጨፍኖ ጭለማን ውስጥ.... እናንተ ስትጸልዩ ከፊት ለፊታችሁ ያለውን ቁስ ንገሩንና የናንተ ከኛ ስዕል የተሻለ እንደሆነ አሳምኑን እስኪ። መቼም ከፊት ለፊታችሁ ያለን ግዙፍ ግድግዳ፣ ወይም ጭለማ አልፈ በአይነ ህሊናዬ ጌታን እያየው ነው የምጸልየው ልትሉ እንደምትችሉ እናምናለን። ታዲያ የናንተ ይህን ማድረግ ትክክል እንደሆነ ማመን ከቻላችሁ፣ የኛን በስላሴ ስዕል ፊት ቆመን ህሊናችንን ወደ ሰማያዊው የስላሴ መንበር ነጥቀን ጸሎት ማድረጋቸችን እንዴት ስህተት ሊሆን ይችላል?



በስዕሉ ባለቤት በሰላሴ ፊት መቆችንን እያሰብን የአምልኮ ስግደት ብንሰግድ ጥፋቱ ምንድነው? በድንግል ማርያም ስዕል ፊት ቆመን፣ በአይነ ህሊናችን እርሷን እየተመለከትን ለርሷ ያለንን ፍቅር በትህትናና በስግደት መግለጽ በምን ዓይነት መንገድ ጣዖት ማምለክ ሊሆን ይችላል? በዓለም ዙሪያ ያሉ ክርስቲያኖች (ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ እና ከፊል ፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች) ስዕልን ለትምህርት፣ ለጸሎትና ለስርዓተ አምልኮ ይጠቀማሉ። ነገር ግን አንዳቸውም በስዕሉ በኩል የስዕሉን ባለቤት ለመቅረብ እንጂ፣ ተቃዋሚዎች እንደ ሚገልጹት ስዕሉንና የስዕሉን ባለቤት ለይተው አያዩም። ስዕሉን ከባለቤቱ ለይቶ የሚያመልክ ክርስቲያን በዓለም አንድ እንኳን አይገኝም። እንግዲህ የሁለት ዓለም ሰዎች የሆነው፤ በዓለም ላይ ያለን በቢሊዮን ምንቆጠር ክርሰቲያኖች ስለተሳሳትን ነው? ወይስ ፕሮቴስታንተት ስለስዕል የተሳሳተ አመለካከት በመያዛችሁ ነው?

በስዕል ፊት መስገድ ለስዕሉ ባለቤት መስገድ ነው። በስላሴ ወይም በጌታ ስዕል ፊት የአምልኮ ስግደት እንሰግዳለን። በመላእክት ወይም በቅዱሳን ስዕል ፊት በትህትናና በፍቅር ሆነነ ለስዕሉ ባለቤት የአክብሮት ስግደት እንሰግዳልን። ለማን እንደምንሰግድና ምን ዓይነት ስግደት እንደምናቀርብ የምናውቀው እኛው ነን። አንድ ሰው በቅዱሳን ስዕል ፊት ስሰግድ እያመለካቸው ነው ቢለኝ፣ ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው እለዋለው። የትኛውን ዓይነት ስግደት አየሰገድኩ እንደሆነ እርሱ ሳይሆን የማውቀው እኔ ስለሆንኩ። በሐዲስ ኪዳን ለመላእክት መስገድ እንደማይገባ መልአኩ የሐንስን አስጠንቅቆ ነግሮታል የሚሉም ይኖራሉ። እኔም እንዲህ መልስላቸዋል። መልአኩ በትህትና አትስገድ ማለቱን ሳይሆን፣ ዮሐንስ በፍቅርና ባክብሮት ሆኖ፣ ደጋግሞ መስገዱን አብነት አደርጋለው። እንደ ዮሐንስ ለመልአኩም ደጋግሜ በአክብሮት እሰግድለታለው። ራዕ. 19፣10፣ ራዕ.22፣8። ለቅዱሳንም የሚደረግ ስግደት ምንጩና ዓላማው አክብሮት እንጂ አምልኮ አይደለም። በፍጹም!!! የሚከተሉትንም የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች መመለከት የአክብሮት ስግደት ምን እንደሆነ ለመረዳት ይጠቅማል። (ዘፍ. 27:29; 33:3-7; 37:10; 41:43; 42:6; 43:26; 47:31; 48:12; 49:8; ሩት. 2:10; 1 ሳሙ. 20:41; 24:8; 25:23, 41; 28:14; 2 ሳሙ. 9:8; 14:22, 33; 18:21; 24:20; 1 ነገ.1:15, 23, 53; 2:19; 2 ነገ. 2:15; 4:37; 1 ዜና. 21:21; አስቴ. 3:2)

ቅዱሳት ስዕላት ተዓምራትን ማድረግ ይችላሉን? ብለው ለሚጠይቁን እኛም ጥያቄውን በጥያቄ እንመልሳል። የሙሴ በትር ባህርን መክፈል፣ ሙሴ በዓላማ የሰቀለው እባቡ እስራኤልን ከበሽታቸው መፈወስ፣ ታቦቱ ዮርዳኖስን መክፈል፣ የኤልሳ አጽም ሙት ማስነሳት፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ጥላ ሙት ማስነሳት፣ የቅዱሳ ጳውሎስ የልብሱ ድውያንን መፈወስ....ይችላልን ብለን እንጠይቃለን። መልሱም ምን እንደሆነ ለማናችንም ግልጥ ያለ ነው።

5. ስዕልና ክርስትና

ከክርስትና መመስረት ጀምሮ ስዕል በቤተክርስቲያን ታላቅ አስተዋጽኦ አለው። ከዚያን ዘመን ጀምሮ ወንጌል በቃልም፣ በጽሑፍም በስዕልም ተሰብኳል። ስዕል በኦሪቱም በሐዲስ ኪዳንም የነበረን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክስተት የሚገልጽ ብቻ አይደለም። የእግዚአብሔርን ቃልና ሰማያዊው ስርዓትም በዓይነ ህሊናችን እንዲሳል የሚረዳን ጭምር አንጂ። በክስርትናው ዓለም ስዕል እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሀ ፈሳሽ ድንገቴ የሆነ ክስተት አይደለም። ክርስትናን ከራሱ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ እግር ስር ቁጭ ብለው፣ የአንደበቱቱ ትምህርት ከሰሙት የእጁን ተዓምራት በአይናቸው ካዩት ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የነበረ እና ያለ ህያው ታሪክ ነው። ክርስትናን ባደባባይ መመስከር በማይቻልበት ዘመን ሐዋርያት በካታኩምቦ ዋሻ ወንጌልን ያስተምሩ፣ የነበረው በድብቅ ተሎታቸውን ይፈጽሙ የነበረው በስእል አማካኝነት ነበር።

ስዕል መጽሐፍ ቅዱስና ባልነበረበትና የጽሑፍ እውቀት ባልተስፋፋበት ዘመን ጀምሮ ስነጽሑፍ እስከ ተስፋፋበት ወርቃማው ዘመን ድረስ ወንጌል ለመስበክ እንደ ድልድይ የነበረም ነው። የጽሑፍ እውቀት ያልነበራቸው በቃል ሰዎች በቃል ከመማራቸው በተጨማሪ ወንጌልን የተማሩበት የተረዱበት በስዕል አማካኝነት ነበር። የለጥርጥር የጽሑፍ እውቀት ላለነበራቸው ክርስቲያኖች ስዕል መጽሐፍ ቅዱሳቸው ነበረ፤ ነውም። ወንጌልን በልባቸን ለመቅረጽ በአይናቸው ፊት የተሳለው ስዕል ታላቅ አስተዋጽኦ አለው።

የስዕል ዓላማውም ወንጌልንና የስዕሉን ባለቤት ፍቅር በልባችን እንዲሳል መርዳት ነው። ዮሐንስ ደማስከስ የተባለ አባት “በቅዱሳተ ስዕላት አማካኝነተ ህሊናችን ወደ ሰማያዊው የቅዱሳን ህብረት ይነጠቃል” ይገልጻል። (PG 94:1261a). ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙም አብርሐም ይስሀቅን የሚሰዋበትን ስዕል ስመለከት አይኖቼ በእንባ ይሞላሉ በማለት ገልጿል። (PG 46:572). ጳውሎስ ለዚህ ነው የገላትያ ከርስትያኖችን “የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው” በማለት የገሰጸው። ገላ.3፣1። በክርስትና ታሪክ ቅዱሳት ስዕላትን መጠቀም የጀመሩት የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ናቸው። እመቤታችን ልጇን ታቅፋ የምናያትን ስዕል ለመጀመሪያ ጊዜ የሳለው ወንጌላዊው እና ሰዓሊው ሉቃስ ነው። የጌታን የስቅለት ስዕል የሳለው ደግሞ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው። ይህንን አውነት የታሪክና የትውፊት ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ። ይህንን ይበልጥ መመርመርና መረዳት የፈለገም ከቤተክርስቲያችን መጻህፍት በተጨማሪ፣ ጥንታውያን የክርስትና መጻሕፍትን፣ የኦርቶዶክስና የካቶሊክ ኢንሳይክሎፒዲያዎችን እንዲሁም ዊኪፒዲያና ተመሳሳይ የመረጃ ምንጮች ላይ መመልከት ይቻላል።

በክርስትናው ታሪክ አብዛኛዎቹ ጥንታውያን አባቶች ስለ ስዕል በዙ ተናግረዋል ጽፈዋልም። የሐዋያው ዮሐንስ ደቀመዝሙር ሰማዕቱ ፖሊካርፐስ (The Martyrdom of Polycarp 17:2-3; 18:1-3) ቅዱስ ሄራኒየስ (St. Irenaeus: AD. Haer. 1:24, 25)፣ ታዋቂው የመጀመሪያው መቶ ክ.ዘ. ታሪክ ጸሐፊ ቱርቱሊያን (Tertullian: De Pudicitia 7)፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር ቅዱስ ቀለሜንጦስ (Clem Alex. : Protrepticon 1 : 62)፣ ኦሪገን፣ አውሳብዮስ (Eusebius: H.E. 9:9; Vita Constantine 3:49)፣ ቅዱስ ፓውሊኒዮስ፣ (St. Paulinus of Nola : Epistle 32:17), ቅዱስ ባስልዮስ ፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፣ ወዘተ.... እኒህ ሁሉ አባቶች ስለ ስዕል የጻፉልንን መዘርዘር ቅዱስ ጳውሎስ ሁሉንም እንዳልተርክ ጊዜ ያጥርብኛል እንዳለው ይሆንብናል። ሰለዚህም በጥልቀት ጥናት ማድረግ ማወቅ የፈለገ ሰው የአባ ታድሮስ ማላቲን - THE CHURCH HOUSE OF GOD- መጽሐፍቸውንና በህዳግ የተጠቀሱትን ሌሎች በርካታ መጻህፍት ከሌሎች የኢንተርኔት መረጃዎች ጋር በማጣመር አንድ መጽሐፍ ሊወጣው የሚችል ብዙ እውቀት መሸመት ይቻልል። እኔ ግን ከዚ በላይ እንዳልሄድ ጌዜ ገደበኝ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!!

==== ታሪኩ ወዳጆማማማማም

ፀ ሃይማኖት ተዋህዶ

ምዕራፍ ሰባት

፮. ቅዱሳት ሥዕላት

በዚህ ርእሰ ሥር ስለ ቅዱሳት ሥዕላት ምንነት፣ ጥቅም /አገልግሎት እንመለከታለን። በርእሰ ለተቀናበረው ምላሽ መነሻችን በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ላይ የነፍሩ ጥላቻ ያለው ጸሐፊ «የማርያም ሥዕል /ሥዕለ አድኅኖ/ የሚባለው ከየት መጣ» ገጽ 107 በማለት በአጠቃላይ በቅዱሳት ሥዕላት ላይ ያስተላለፈውን ኑፋቄ ለማረም ነው።

፮.፩. ቅዱሳት ሥዕላት ለምን «ቅዱሳት» የሚል ቅጽል ተሰጣቸው?

በቅድስት ቤተክርስቲያን ለመንፈሳዊ አገልግሎት፣ ትምህርት እና ስብከት የምንገለገልባቸው የጌታችንን፣ የእመቤታችን የቅዱሳን መላእክት፣ ሐዋርያት፣ ጻድቃን እና ሰማዕታት ሥዕላት የሥጋዊውን ዓለም ገጽታ ከሚያንጸባርቁ ዓለማውያን ሥዕሎች የተለዩ በመሆናቸው ቅዱሳት ሥዕላት ተብለው ይጠራሉ። ዓለማውያን ሥዕላት አእምሮን የመሳብ፣ መልክት የማስተላለፍ እና የማስተማር አቅም ቢኖራቸውም እንደ ቅዱሳት ሥዕላት ተአምር የማድረግ እና ሀረክት የማስተላለፍ አቅም የላቸውም። ቅዱሳት ሥዕላት ግን የተመከለባቸው ቅዱሳን መልእክት ያስተላልፉባቸዋል ተአምር ያደርጉባቸዋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የእግዚአብሔርን የልግስናውን ብዛት ሲገልጥ «እግዚአብሔር መንፈሱን /ጸጋውን/ ሰፍሮ አይሰጥምና» (ዮሐ. ፫፡፴፬) ሲል እንደተናገረው በእግዚአብሔር ኔጋ የተነበኑ ቅዱሳን የሰውነታቸው ቅድስና በልብሳቸው የልብሳቸው በጥላቸው አልፎ ልዩ ተአምር እንደሚሠራ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። የሙሴ በትር (ዘፀ. ፬፡፲፱)፣ የኢልያስ መጎናጸፊያ (፪ነገ. ፪፡፰)፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ጥላ (የሐዋ. ፭፡፲፭-፲፮) የቅዱስ ጳውሎስ ልብስ (የሐዋ. ፲፱፡፲፪) ተጠቃሽ ናቸው። የቅዱሳን ቅድስና በጥላቸው አልፎ ሕመማን እንደሚፈውስ የተመከለበት

ሥልጣ ቅድስናቸው ተላልፎ ሕመማንን የመፈወስ ጋኔን የማራት ኃይል አለው። በዚህ መሠረት ቅዱሳት ሥዕላት የቅዱሳን ቅድስናቸው ተገልጸባቸው ገቢረ ተአምራት የሚያደርጉ በመሆናቸው ከሌሎች ዓለማውያን ሥዕላት መለየታቸውን ለመግለጽ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ቅዱሳት ሥዕላት በማለት ትጠራቸዋለች።[105]

ቅዱሳት ሥዕላት ጸጋ እግዚአብሔር የሚያድርባቸው በመሆናቸው ክብር ይሰጣቸዋል። በፊታቸው ቆሞ መጸለይና መስገድ መናፍቃን እንደሚሉት ሥዕልን ፈጣሪዬ ማለት አይደለም። ቁም ነገሩ ከሥዕሉ ባለቤት በረከትና ረድኤት ለማግኘት የሚደረግ የእምነት ግዙ ነው። ሥዕሉ የጻድቁ ወይም የቅዱሱ መታሰቢያ ነው (ምሳ. ፲፡፯)።

፮.፪. የቅዱሳት ሥዕላት ታሪካዊ አመጣጥ

ቅዱሳት ሥዕላት መሠረታዊ መነሻቸው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር ቀደም ብሎ «ሕገቤ»፣ እያለ ለሚጠራቸው እስራኤላውያን መንፈሳውያት ሕግጋትን ሲሠራ የቅዱሳት ሥዕላትን አነገግሎትና ጥቅም በግልጽ ለነቢያት በመግለጽ ቅዱሳን ነቢያት ትእዛዙን ገቢራዊ አድርገዋል። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ነበግ እረኝነት ለነቢይነት የጠራውን ሙሴን «ሥዕለ ኪሩብን» በታቦተ ሕጉ ክዳኑ ላይ እንዲሥል ሲያዝዘው «ከሥርየት መክደኛው ጋር እንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን ሁለተኛውንም ኪሩብ በሌላ ወገን አድርገህ በአንድ ላይ ትሠራዋለህ» ብሎታል (ዘፀ. ፳፭፡፲፱)። ሥዕላቸው በጽላተ ኪዳኑ፣ በታቦተ ሕጉ ላይ እንደሚናተፉ ዶሮዎች ተደርገው እንዲሣሉ የተደረጉት «ኪሩቤል» ቀደም ብሎ የሚገለባበጥ ሰይፍ ይዘው የኅጎትን ደጃፍ እንዲጠብቁ የታዘዙት ናቸው(ዘፍ. ፫፡፳፬)። እነዘህ በሙሴ እንዲሣሉ የታዘዙት ሥዕላተ ኪሩቤል የጻወርተ መንበር አምሳያዎች ናቸው። ይህ ታሪክ የቅዱሳት ሥዕላት ሥራ መሥራች ባለቤቱ እግዚአብሔር መሆኑን ያስገነዝባል። ቤተመቅደስን በቅዱሳት ሥዕላት የማስዋብ ተግባር በእግዚአብሔር በታዘዙ ነቢያት እጅግ ተስፋፍቶ እንደነበር የብሉይ ኪዳን የታሪክና የትንቢት መጻሕፍት ያስረዳሉ። ለአብነት የሚከተሉትን

[105] ቀሲስ ደጀኔ ሽፈራው፣ ነገረ ቅዱሳን /አዲስ አበባ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ገጽ ፴፱።

ጥቅሶች ይመልከቱ። (ነገሥ.ተዳ. ፮፥፳፫፣ ሕዝቅ. ፱፥፫፣ ፲፥፫፣ ፲፩፥፳፪ -፳፫፣ ሐዋ. ፲፬፥፲፯፣ ዘፀ. ፳፭፥፳)።

፮.፫. ቅዱሳት ሥዕላት በቤተ ክርስቲያን

ሥዕል በቤተክርስቲያን የቆየ ታሪክ ያለው መንፈሳዊ የጥበብ ዘርፍ ነው። የክርስትና ሃይማኖት ከተስፋፋባቸው መንገዶች አንዱ ቅዱሳት ሥዕላትን፣ ሕማማተ መስቀልን፣ ግፍአ ሰማዕታትን /ሰማዕታት የተቀበሉትን ግፍ/፣ በምሳሌ ለማስተማሪያነት በማዋል ነው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በቅዱሳት ሥዕላት እንዴት እምነታቸውን እንዳስፋፉ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፈው አባ ጎርጎርዮስ ሲያብራሩ፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደተገለጠው የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ትምህርታቸውን ያስፋፉት ዋሻ ፈልፍለው ጉድጓድ ቆፍረው በዋሻ በፍርክታ ውስጥ ነው። ኪታበ ምግባብ ፖዝበ ምዮሪ/ ይሉታል። በዚህ ዋሻ ውስጥ የሰማዕታትን ሰም እየሰበሰቡ ጸሎት እየጸለዩ ትምህርት ያስተምሩ ነበር። በዚህ ውስጥ ብዙ አማኞች እየመጡ የማኅበራቸው አባል መሆን ጀመሩ። በዚያን ጊዜ የክርስትናን ትምህርት አስፋፍቶ ለመስጠት በቂ መጻሕፍት አልነበሩም። እንደልብ ወጥቶ ለመፈለግና ለማዘጋጀት ነጻነት አልነበራቸውም፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ምሳሌዎችን በሥዕል እየሠፈሩ ማስተማር ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ ማስተማሪያ ሆኖ ቆይቷል። ሥዕሉትም የሚሣሉት በምሳሌነት «ሲምቦል» ሲሆን የሚሳሉትም በአመድና በአክል በዋሻው ዙሪያ ነው። በዋሻው ፊት ሰፊት ለአፈ ጽዮን/ የሚሳሉት አረኖው በጉን እንደተሸከመ አድርገው ነው። «ክርስቶስ ያመኑበትን ሁሉ በስሙ አምነው የሞቱትን ሁሉ የሚያድን ቸርና ታማኝ መሆኑን ለማስረዳት ነው። ሊሳሉ ሥዕላቸውን የሚጀምሩት በብሉይ ኪዳን ታሪክ ነው»[106] ብለዋል።

ቅዱሳት ሥዕላት በቤተክርስቲያን አገልግሎት እና በምእመናን ሕይወት የሚያሳድሩት በጎ ተጽዕኖ አለ። ይሆንን ሁኔታ ዮሐንስ ዘደማስቆ የተባለ ምሁር በሁለት ከፍሎ ሲያብራራ፦ ሥዕል በቤተ ክርስቲያን

106. አባ ጎርጎርዮስ፣ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ። ፲፱፻፹፱ ገጽ ፩፻፲-፩፻፲፩።

አሳት ዓይነት ጥቅም አለው። ከነዚህም አንዱ በዋሻ እንደነበሩት ክርስቲያኖች ተአምራት ነክ የቅዱሳት መጻሕፍትን ታሪኮች ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ለማስረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሃይማኖቱን ሳይፈራ ሳያፍር መስከር በሰማዕትነት የሞተ ወይም ስለ ዓለምና ስለ ራሱ በመጸለይ መሰ ሕይወቱን ከፍትውት ከእኩያት፣ ከአጋንንት ጋር በመጋደል ያሳለፈውን ለማሰት ወይም ጻድቅ በሥዕሉ ለማስታወስ በሥዕሉ አማካኝነት አያንዳንዱ ምእመን ለሥዕሉ ባለቤት ያለውን ክብርና ፍቅር ለመግለጥ ነው ብሏል።[107]

ከላይ በቤተ ክርስቲያን ሊታውንት ማብራሪያ እንደተሰጠው ቅዱሳት ሥዕላት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያስወሰናቸው በቅዱስ መቅደሱ በክብር በሚቀመጥ ታቦተ ኪዳን እና ጽላተ ኪዳኑ ላይ እንዲሣሉ የፈቀደ እግዚአብሔር ነው። በዚህ ፈቃድ መነሻነት ምእመናን ለሥዕሉ ባለቤት ያላቸውን ፍቅር እና ክብር በመሳም /በመሳለም/ በሥዕሉ ፊት በመጸለይ ይገልጣሉ። ይህን በፍቅር ላይ የተመሠረተውን መንፈሳዊ ድርጊት አንዳንድ ወገኖች «ለጣዖት መስገድ ጣዖት መሳለም ነው» ብለው ይከራከራሉ። በሥዕል ፊት መስገድና ሥዕሉን ለጣዖት መስገድ አይደለም። ምክንያቱም ሥዕለ ኪሩቤል የተሣለበት ታቦትና ጣዖት ምንም ዓይነት ተዛምዶ እንደሌላቸው፣ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የብርሃንና የጨለማ ያህል እንደሚለያይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲያስረዳ «ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ቶስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔርን ታቦትስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማነው?» ብሏል /፪ቆሮ. ፮፥፲፭-፲፮/።

፮.፬. የሥዕልና የምስል ልዩነት

አንዳንድ ጸሐፊዎች ለሥዕልና ለምስል አንድ ዓይነት ትርጉም በመስጠት ጽፈዋል። ነገር ግን በሥዕልና በምስል መካከል መሠረታዊ ልዩነት አለ። በተለይም ቅዱሳት ሥዕላት በአብያተ ክርስቲያናት

107. ገጽ. ከሚው ገጽ ፩፻፲፩።

ግድግዳ፣ በሸራ፣ በብራና፣ በወረቀት፣ በጨርቅ እና በሌሎች ለመሣል አመቺ በሆኑ ነገሮች በቀለም የሚሣሉ በወይን የሚታዩ በእጅ የሚጻፉ ናቸው። ቅርጽ ወይም ምስል ግን ከሥዕል በተለየ ሁኔታ በድጋይ፣ በእንጨት በብረታ ብረት በመሳሰሉ ነገሮች ቅርጽ ወጥቶለት የሚሠራ ነው። እነዚህን መሠረታዊ ልዩነት ያላቸውን ነገሮች አንድ ዓይነት ትርጉም ሰጥቶ መጻፍ ለከሩ ስሕተት ያጋልጣል። ወይም ሁለቱን ነገሮች እንድ ጊዜ ሥዕል ሌላ ጊዜ ምስል እያሉ መጻፍ የመናፍቃን የማጻናገሪያ ስልት ነው። ለምሳሌ በትዱላት ሥዕላት ላይ ነቀፌታ ለመሰንዘር የተነሣው ጸሐፊ «ጽሑፉን ሲጀምር «የማርያም ሥዕል» /ሥዕለ አድኅኖ/ ገጽ 107 ላይ በማለት ይጀምርና በገጽ 111 ላይ ከላይ የሰጠውን ስያሜ ገልብጠና ከዶ «በኢትዮጵያ ውስጥ «የሥዕላተ አድኅኖ» ምስሎችን ማከበር በእርሱ መታመንና የሥዕላቱ ተፈላጊነት እያደገ የመጣው ከዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ወዲህ ነው» ብሏል። ጸሐፊው «ሳኒተ ክርስቲያንን ሥዕሎች ሥዕላተ አድኅኖ» ብሎ በጀመረበት ጽሑፍ ወይም አገለላጽ አልቀጠለም። ምክንያቱን ለምን ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር ጸሐፊው «የበግ ለምድ የለበሰ ነጣቂ ተኩላ»በመሆኑ ነው። /ማቴ. ፯፡፲፭/

፯.፫. ሥዕለ አድኅኖ

በቤተክርስቲያን የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ የቅዱሳን ሰምችና መላእክት ሥዕላት ገቢረ ተአምር አድራጊ በመሆናቸው ሥዕለ አድኅኖ ተብለው ይጠራሉ። ቅዱሳት ሥዕላት የተለየ ገቢረ ተአምር ያደርጋሉ። ለምሳሌ ከ14-37 ዓ.ም ርምን ይገዛ የነበረው ጢባርዮስ ቄሣር ለዙፋን የደረሰ ልጅ ቢሞትበት አስከሬኑን ወደ ኢየሩሳሌም ልኮ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር እንዲጥሉት ቢያደርግ የሞተው ወጣት ልጁ ተነሥቷል። ንጉሡ ጢባርዮስ ከደስታው የተነሣ የዚህን ሰው እናቱን አምጡልኝ፣ እኔም ሚስቴም እናንልግላት ብሎ ሰው ቢልክ የእመቤታችን ክብሯ ሰማያዊ እንጂ ምድራዊ ባለመሆኑ ተሠውራብቸው አላገኙአትም። ጢባርዮስ ተስፋ እንዳይቆርጥ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ

እናቱው አድርጎ ከለሚዳ አስታጥቆ ሥሉታል። ስለ ሥዕሉ እውነተኛነት ለማረጋገጥ ቅዱስ ዮሐንስ የሣለው ሥዕል፣ «አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደሰቀሉኝ እንተ ደግሞ ሁለተኛ በሮም ሰቀልከኝ» የሚል ድምፅ አሰምዕ ቅዱስ ዮሐንስ ሥዕሉን ቢሰመው ከንፈሩ ከሥዕሉ ጋር ተጣብቆ ፈቷል። ይህ ሁሉ ከሥዕሉ የታየው ተአምራት ነው።»[108]

ደሀንን ሁኔታ «የመልከአ ኢየሱስ» ደራሲ ሲያብራራ «ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ዮሐንስን ለሳመ መለኮታዊ አፍህ ሰላምታ ይገባል። የልቡናው ንጽሕና ሚዜነቱ ተወዳጅነት አግኝቷልና»[109] ብሏል። ጸደ.ንያ በሚባል ሀገር እንጎንን በመቀበል መንፈሳዊ አገልግሎት ትሰጥ የነበረችው ማርታ ምትባል ሴት ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ለመሣለም የሚጓዘውን ሰው ሥዕለ ማርያምን እንዲገዛላት ትልከዋለች። መነኩሴው ሥዕሉን ገዝቶ ሊመለስ በመንገድ ወንበዴዎችና የዱር አራዊት አደጋ ሊያደርሱበት ሲቀርቡ ሥዕሏን ሲያሳያቸው ሸሽተው ወደ መጠዝት ይመለሳሉ። መነኩሴው በዚህ በተደረገለት ተአምር በመድኃኔት የገባውን ቃል ኪዳን አፍርሶ ሥዕል እንዲገዛላት ከላከችው ሴት ዘንድ ሳይደርስ በሌላ መርከብ ተሳፍሮ ሊሔድ ማዕበሉ የመርከቡን አቅጣጫ አስለውጦ ጸደ.ንያ ይደርሳል።

በመንገድ ላይ ሥዕሏ ያደረገችለትን ተአምር ተናግሮ ለማርያም መንጌላዊ ቅዱስ ሉቃስ የሣላትን ሥዕል ማስረከቡን ተአምረ ማርያም ይነግረናል።[110] ሊቀ ጳጳስ አባ ዮሐንስ በጻፈው ድርሳነ ሚካኤልም የአስተራኒቆስ ሚስት አርምያ በሥዕለ ሚካኤል ዲያብሎስን ማባረሯን ሲያብራራ «አርምያም እንተ ሚካኤል ከሆንክ በእኔ ቤት እንዳለ እንደ ሚካኤል ሥዕል አምሳል ምልክት ያለበት በትር ወይስ አለ?» አለችው. . . ወዲያውኑ የክፋ የዲያብሎስ ፊት ተለውጦ እንደጨለማ ተራራ ሆነ[111] ይላል።

ሊቀ ጳጳስ አባ ዮሐንስ በቅዱሳት ሥዕላት ፊት ስለ መስገድ ሲያብራሩ «በተቀደሱ ሥዕላት ፊት መጸለይን፣ ለእግዚአብሔር ስግደትንና ምስጋና ማቅረብንም ቸል አትበል፣ በእነርሱ ላይ የሚገለጠውን የእግዚአብሔርን

ሥራ አትጠራጠር» ብለዋል። በቅዱሳት ሥዕላት ፊት መስገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑንም ሲያስረዱ ደግሞ «ግስተ-ሥረያው ላይ ሩበው ከነበሩት ከመመስገኛው ኪሩቤል መካከል እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን ይገለጥ ነበርና። ከእጃቸው ከቃላቸውም ምስጋናን መሥዋዕትን ጸሎትን ይቀበል ነበርና የሕዝቡንም ኃጢአት ያስተሠርይ ነበርና ይህም ረቂቅ ድንቅ ለሆነው ምስጢር ምልክት ነው። ስለዚህ በተቀደሱ ሥዕላት ፊት ጸሎትን ለሚቀበል ሕይወትን ለሚያድል ለአብር ባለቤት ምስጋናን ምልጃን ጸሎትን ያቀርቡ ዘንድ ለምእመናን ሥርዐት ሆነ።»

«በሰማይ ካለው በምድርም ካለው ከምድር በታች በውኃ ውስጥ ካለው ፍጥረት ሁሉ ለአንተ አምላክ አታጉበድ። አትስገድላቸው አታምልካቸው ሲል እግዚአብሔር አዝዟል። ስለዚህ በተቀደሱ ሥዕላት ፊት ለእግዚአብሔር ጸሎትንና ምስጋናን ማቅረብ አይገባም» እያሉ በአሪት ቃል የሚያመካኙ ወገኖችን ሲወቅስ እኛም የአሪትን ቃል ጠንቅቀው እንዲያስተውሉ እንመክራቸዋለን፤ ቃሉ አትስገድላቸው አታምልካቸው ይላልና። እነዚህ ጣዖታትም የተናቱ የተዋረዱ ናቸውና። እነርሱ በልዩ ልዩ መልክና ምሳሌ የሚሠሩ ጣዖታት ናቸው። ለእነርሱ ልንሰግድላቸው አይገባም። ሰው ሠራሽ ናቸውና የእግዚአብሔር ኃይልም የለባቸውምና። ቅዱሳት ሥዕላት ግን እንደነዚያ አይደሉም። የምስጢር ምልክቶች ናቸው እንጂ። የሰው ጎሊና በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ያርፍ ዘንድ ረዳት የሚሆኑ፣ረቂቅ ምስጢርንም ማለት የእግዚአብሔር ልጅ ሰው እንደመሆኑ ከድንግል እንደመወለዱ በበረት እንደመተኛቱ በዮርዳኖስ እንደመጠመቁ በመስቀል ላይ እንደመሰቀሉ እንደ ትንሣኤው እንደ ዕርገቱ ዳግመኛ በጊትነት እንደመምጣቱ ያለውን የሚያሳይበት ድንቅ የሆነ የእግዚአብሔር የሥራው መጻሕፍት ናቸው እንጂ።[112]

፭.፮. በቅዱሳት ሥዕላት የሚደረጉ ገቢረ ተአምራት

አስተድመን እንደተመለከትነው የቅዱሳን የነፍነታቸው ቅድስና ለሰውነታቸው የሰውነታቸው ለልብሳቸው የልብሳቸው ለጥላቸው ተላልፎ ተአምር

112. ዝኒ ክሣሡ ገጽ ርያሟ።

እንደሚያደርግ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘረገራል። [መጽሐፈ ነገሥት ፪፥፭ ፪፰ በሰፋት እንደሚተርከው ነቢዩ ኤልያስ የእግዚአብሔር ጥሪ ደርሶት ወደ ገለሬ ሕያዋን ሲያርግ የዮርዳኖስን ወንዝ ከፍሎ የተሻገረበትን መጎናጸፊያውን ለደቀ መዝሙሩ ኤልሳዕ ሰጥቶታል። ነቢዩ ኤልሳዕ መምህሩ ኤልያስ በሰጠው መጎናጸፊያ ፈለገ ዮርዳኖስን ቢመታው ባሕሩ በተአምር ለሁለት ተከፍሎለት ዮርዳኖስን ተሻግሯል። የማንኛውም ሰው መጎናጸፊያ ባሕሩን ቢመታ ባሕር የመክፈል ውኃን ከትሮ የማቆም ኃይል አይኖረውም። «እግዚአብሔር በወዳጆቹ በቅዱሳን አድሮ ድንቅ ሥራውን ይሠራል» [መዝ. ፷፰፥፴፭] ሲል ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት እንደተናገረው የነቢዩ ኤልያስ ቅድስና በመጎናጸፊያው ስላለፈ በመጎናጸፊያው ተአምር ሲደረግ ችሏል። ለአንዳንድ ወገኖች ይህ ደረቅ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ ሲነገራቸው ይህ የቆየና በብሉይ ኪዳን የተደረገ ነው ብለው ይከራከራሉ። እነርሱ ይህን ይበሉ እንጂ በቅዱሳኑ አድሮ ተአምር የሚሠራ እግዚአብሔር ምንጊዜም አዲስ ነው። ሥራውም የትላንት የዛሬም ነው እግዚአብሔርም የትላንትም የዛሬም አምላክ ነውና (ዕብ. ፲፫፥፰)። እንግዲህ የቅዱሳን ቅድስና በማዕዝ ልብስ እና በረቂቅ ጥላ ከተላለፈ በሥዕላቸውማ ምን ያህል ተአምር ያደርጉ ይሆን? ከዚህ አንጻር ቅዱሳት ሥዕላት በርካታ ገቢረ ተአምራትን እንደሚያደርጉ የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

፭.፮.፩. ቅዱሳት ሥዕላት ይናገራሉ

አንዳንድ በእምነት ያልጠነከሩ ሰዎች እንዴት ሕይወት ከሌላቸው ግዑዝ ነገር ድምፅ ይወጣል? ንግግርስ እንዴት መስማት ይቻላል? ብለው ይጠይቃሉ? መጽሐፍ ቅዱስን ግን በጥልቀት ስናነበው በእግዚአብሔር ፈቃድ የማይናገሩ ግዑዛን ድንጋዮችና መናገር የማይችሉ እንስሳት እና አፍ ያልፈታ ሕፃናት አንደበት አውጥተው እንደሚናገሩ ይገልጣል። ለምሳሌ በዕለተ ሆሣዕና ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ በብዙ አጀብ ሲገባ ፈሪሳውያን ጀርባ ታዝለው የመጡ የአርባ እና የሰማንያ ቀን ሕፃናት ድንጋዮች ቢያመሰግኑ ዐይተው ከአናቶቻቸው ትንሽ እየወረዱ ሰሌን እየቆረጡ ይዘው አመስግነዋል።[113]

113. ወንጌል ቅዱስ ማቴዎስና ትርጓሜው ገጽ ፻፶፬።

እንዲሁም በአሪት (ዘኁ. ፳፪፥፳፩-፴) በተመዘገበው ታሪክ ውስጥ እንደምናነበው የበለዓም አህያ መናገር የማትችል የቤት እንስሳ ስትሆን እግዚአብሔር ተአምር እንዲደረግ በፈቀደ ጊዜ በሰው አንደበት ጌታዋን ለማነጋገር በቅታለች። የአህያይቱንና የበለዓምን ንግግር መጽሐፈ አሪት ሲያስነብበን «እግዚአብሔር የአህያይቱን አፍ ከፈተ፥ በለዓምንም ሦስት ጊዜ የመታኸኝ ምን አድርጌብህ ነው? አለችው። በለዓምም አህያይቱን ስላሳገጥሽብኝ ነው፥ በእጄስ ሰይፍ ቢኖር አሁን በገደልኩሽ ነበር፥ አህያ ይቱም በለዓምን ከብዙ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የምትቀመጥብኝ አህያህ አይደለሁምን? በውኑ እንዲህ አደርግ ዘንድ ልማዴ ነበረን? አለችው። እርሱም እንዲህ አላደረግሽ ብኝም አላት። እግዚአብሔርም የበለዓምን ዐይኖች ከፈተ። የእግዚአ ብሔርን መልአክ በመንገድ ላይ ቆሞ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ ወየ፥ ሰገደም በግምባሩም ወደቀ» ይላል (ዘኁ. ፳፪፥፳፭-፴)።ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በአሪት የተጠቀሰውን ተአምራዊ ታሪክ በመጥቀስ ትንኑት የጎደለው ተግባር የሚፈጽሙ ሰዎችን ሲወቅስ «ትንን መንገድ ትተው ተሳሳቱ የባሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ፥ እርሱ የዓመጻን ደመወዝ ወደደ ነገር ግን ስለመተላለፉ ተዘለፈ። ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብደት ገለጸ» ብሏል (፪ጴጥ. ፪፥፲፭-፲፮)።

እግዚአብሔር ከላይ የተዘረዘሩትን የተለያዩ ገቢራተ ተአምራት ግዑዛን ድንጋዮችን፣ አህያ እንዲሁም አፍ ያልፈቱ ሕፃናትን ማናገሩ ድንቅ አምላክ ምንም የሚሳነው ነገር የሌለ መሆኑን እንረዳለን። አንዳንድ ወገኖች እግዚአብሔር ለሙሴ «ከሥርዮት መክደኛው ጋር አንዱን ኪሩብ በአንድ ወገን ሁለተኛውን ኪሩብ በሌላ ወገን አድርገህ በአንድ ላይ ትሠራዋለህ» /ዘፀ. ፳፭፥፲፱/ ብሎ ባዘዘው ሥዕለ ቅዱሳን የሚደረገውን ተአምራት ሲቃወሙ በመጀመሪያ ለጣዖት የተነገረውን ወይም እስራኤል ጣዖትን እንዳይከተሉ የተላለፈውን ትእዛዝ ለታቦት አድርገው በማቅረብ ሰዎችን ጥርጥር ላይ ለመጣል ይዳዳቸዋል። ነገር ግን አነሣሣቸው በተሳሳተ መንገድ ስለሆነ የጥፋት ጽሑፋቸው እና ትም ህርታቸው በእውነተኛው ቃለ እግዚአብሔር ላይ የተመሠረተ አይደለም።

እዚህ ወገኖች አንዱ ሥዕል በቅድስት አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ተቀባይነት ያገኘበትን ሁኔታ በተሳሳተ መንገድ ሲገልጹ ምስሉች ደናገራሉ በማለት ጉዳዩን ቀለል አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ። ሰዎች ከእምነት ጋር በተያያዘ የሚቀርብላቸውን ነገር እምነው ተረ ድተው ይቀበሉታል እንጂ በማስፈራራት እንዲያስተምሩ አልታዘዘም፥ ይልቁኑ በማይቀ በሉአቸው አኳሃኋ «ያመኒማችሁን ትቢያ አራግፉትሁ ውጡ» (ማቴ. ፲፩፥፲፫) ተባሉ እንጂ አስፈራሩ አልተባሉም። ይህም ሲባል የራሳቸውን አመለካከት በኃይል ለመጫን የሚጥሩ ወገኖች የሉም ለማለት አይደለም። ሰዎች በኃይል ወይም በማስፈራራት ለጊዜው አንድ ነገር ቢቀ በሉ ውለው አድረው የእውነት ፀሐይ ሲወጣ እውነትን ይፈልጋሉ። ከዚህ አኳያ በቤተክርስቲያን በቅዱሳት ሥዕላት የተደረገውን ገቢረ ተአምራት ከመግለጽ ባሻገር የተለየ ማስፈራሪያ አይደረግም። ይህንን በእምነት የሚደረግ ታላቅ ተአምር ለማወቅ የኢትዮጵያንና የግብጽን አብያተ ክርስቲ ያናት መመልከት ጠቃሚ መረጃን ይሰጣል። በተአምረ ማርያምም የሚከተለው ተጽፏል ::

«በዚያም ቤተክርስቲያን የእመቤታችን ሥዕል ነበረችና ያ ብላቴና ሥዕሊቱን እጅግ ይወዳት ነበር መምህሩ በሔደ ጊዜ ወደ ሥዕሉ ቆሞ እጅ ይነሣትና ቅዳሴዋን ይደግም ነበር። ከዕለታትም በአንድ ቀን ከሥዕሉ ዘንድ ቆሞ ሳለ ሥዕሊቱ ተነጋገረችው። ወዳጄ ሆይ አንተ ከምትወደኝ ይልቅ ፈጽሚ ወድጀሃለሁ። በአንተም ደስ ብሎኛልና በእኔ እመን አለችው ያም ልጅ ከሥዕሉ ቃል በሰማ ጊዜ ፈጽሞ አደነቀ እጅግም ፈራ» ገጽ. 113።

የሚለውን ታሪክ ተአምር ከተአምረ ማርያም የተወሰደ ነው። ይህ ከተአምረ ማርያም ተቀንጭቦ የተወሰደው ተአምር «ቅዱሳት ሥዕላት የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እንደ ሆኑ እንደሚገለጥ ያሳያል»፣ ክርስቲያኖች ቅዱሳት ሥዕላትን የሚቀበሉት «ሥዕሎችን ይናገራሉ በሚል ማስፈራሪያና

አይደለም የእምነታችን ኃይልና ታላቅነት በእነርሱ ስለሚገለጥ እንጂ ። መናፍቃን ግን ይሽንን አጉልተው ጽፈዋል። በተአምረ ማርያም ላይ የተገለጸው ብላቴና ከሥዕሉ ቃል በመስማቱ እጅግ ከመደነቁ የተነሣ መፍራቱን ይገልጣል። በቅዱስ መጽሐፍ የተለየ ተአምር በሚገለጥበት አካባቢ የሚገኙ ሰዎች ከሚያዩት ተአምር የተነሣ የአድናቆት ፍርሐት እንደሚፈሩ ተጽፏል። ለምሳሌ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ «በዚያ ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሚዳ ያደሩ እረኞች፡- የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ በቀረበ ጊዜ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው ሲበራ እነርሱ ታላቅ ፍርሐትም ፈሩ» ይላል /ሉቃ. ፪፥፰-፱/። እንደዚህ ዓይነት ተአምር ሲገለጥ መፍራት ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጥረት የተለመደ ከስተት ነው። ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታችን በባሕር ላይ ሲራመድ ዐይተው መፍራታቸው ተጽፏል (ማቴ. ፲፬፥፳፮)። የብላቴናውም ፍራቻ የሥዕሏን መናገር ዐይቶ ስለሆነ ተገቢ ፍራቻ ነው።

በሥዕሏ ቃል መሰማቱም የማይከሰት ነገር አይደለም። ከላይ በተ ዘረዘሩት ታሪኮች እንደተመለከትነው እግዚአብሔር በተአምር «ቃል የሌለው አህያ በሰው ቃል» /፪ጴጥ. ፪፥፲፮-፲፯/ ካናገረ የክብርት እናቱን ሥዕል እንድትናገር ማድረግ ይሳነዋል ብሎ ማሰብ አይቻልም። የአህያን፣ የድንጋዮችን እና አፍ ያልፈቱ ሕፃናት እንደሚናገሩ ያነበበ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ የቅዱሳት ሥዕላትን መናገርን ለመቀበል አይቸግረውም። የቅዱሳት ሥዕላቱ መናገር የእግዚአብሔርን ተአምር አድራጊነት ይገልጣል እንጂ ለእምነት መቀበያ ማስፈራሪያነት አልዋለም። /አይውልም/

፭.፭.፫. ቅዱሳት ሥዕላት ወዝ እና ዘይት ያፈላሉ

ቅዱሳን አቡዮች በእምነታቸው የጸኑ ምእመናን እና ከዚም በላይ የጹዱ ሕፃናት ከሥዕለ ማርያም ፊት ቆመው ድምፅ እንደሚሰሙ ከሥዕለ ማርያም ጋር እንደሚነጋገሩ በተአምረ ማርያም በስፋት ተጽፏል። አንድ ሕፃን ሥራ ውላ የምትመጣውን እናቱን ሲያገኝ እጅግ እንደሚደሰት ሥዕለ ማርያምን በማየት መንፈሳዊ ሐሴት እንደሚሰማው ሊቁ አባ ጽጌ ድን

ገጸ ሊገልጥ «ዘሙ ይትፈሣሕ ሕፃን ለበ ይፈኪ እሞ፡ እትፈሣሕ እንሰ ሥዕለኪ በርእይ ወተሰልሞ፡ ሕፃን ልጅ እናቱን ባየ ጊዜ እንደሚደሰት እኔም ሥዕልሽን በማየትና በመሰለም እደሰታለሁ»[114] ብሏል። ይህ ምስክርነት ምእመናንን ቅዱሳት ሥዕላትን በማየትና በመሳለም የሚያገኙትን በረከት ያሳያል። በዚህ መልኩ ከቅዱሳት ሥዕላት የሚገኘውን በረከት በስፋት ስለ እመቤታችን ተአምር የሚያወሳው መጽሐፍ /ተአምረ ማርያም/ ሲናገር «ከተአምራቷም ሁሉ ይልቅ ለሁሉ የሚያስደንቅ ሰብለ ስገል በዋሻ ውስጥ ከልጅዋ ከወዳጅዋ ጋር አማኝተው እንዳዩዋት ያች ሥዕል ሥጋን የለበሰች ትመስላለች። ከእርሷም እንባና መዝ ይወጣ ነበር። ከመሂም የተቀቡት ከሚያስጨንቅ ደዌያቸው ይፈወሱ ኦር።»[115] ይላል። እንደ መስፍኑ ጌዴዎን «የነበረ ተአምራቱ ወዴት አለ?» (መሳ. ፮፥፲፫) የሚል ሰው ካለ፡ በትርቡ ኢኤአ ጎዳር ፳፱፻ ቀን ጀምሮ ሕንድ ሀገር በምትገኘው የሶርያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እና በግብጽ ውስጥ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል እንባ እያፈሰሰች መታየቷን በተለያዩ ዝጹ ድር ተመዝግቧል[116]። በተጨማሪም በግብጽ ሀገር ኢኤአ ታኅሣሥ ፳፫ ቀን ፳፻፲ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ክርስ ኑሚው እርግቦች ጋር በኤል ዘይቱን ከተማ በምትገኘው ቤተ ቲያን መታየቷን ሉስ አንጀለስ ታይምስ ዘግቧል። በግብጽ ውስጥ በዚህ መልኩ እመቤታችን ስትገለጥ ከ1968 ኢኤአ ጀምሮ ለአራተኛ ጊዜ መሆኑን እና ተአምሩም በብዙ ሳይንሳዊ መረጃዎች ተደግፎ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዳገኘ በተለያዩ የጥናት መረቀቶች ላይ ቀርቧል።[117]

አንዳንድ ወገኖች ከሥዕለ ማርያም «ወዝ፣ ዘይትና እንባ ይፈላል ወይም ይወጣል» ተብሎ ሲጻፍ ተራ ፈጠራ ወይም አማኞችን ለመሳብ የተደረገ ጥበብ አድርገው ይቆጥሩታል። እውነታው ግን ከእንደዚህ ዓይነት አመለካከት ይርቃል። ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ከባሕር

114. አባ ጽጌ ድንግል ማኅሌተ ጽጌ።
115. ተአምረ ማርያም፣ «በእኔም ማርያም» በግዕዝ አንቀጽ ፲፰ ቁጥር ፫።
116. Http://www.Sevian Church Org
117. See, Egypt Coptic Church The apparition of virgin Mary at al-Zeitun, Egypt in Mary Cop

ያቸው ውኃ ማፍለቅ የማይችሉ ሸውዛን ነገሮች ውኃ ማፍለቃቸው ተአምር ነው። ለምሳሌ በዘፀ. ፲፯፥፫-፮ እንደተጻፈው እስራኤል በቃዴስ በረሐ በተጠሙ ጊዜ «እኛንና ልጆቻችንን ከብቶቻችንንም በጥማት ልትገድሰን ለምን ከግብጽ አወጣሽን?. . . ብለው ሲያንጎራጉሩ እግዚአብሔር ሙሴን፡ - በሕዝቡ ፊት አለፍ፣ ከእስራኤል ሽማግሌዎች ከእንተ ጋር ውሰድ፣ ወንዙንም የመታህባትን በትር በእጅህ ይዘህ ሒድ፣ እነሆ እኔ በዚያ በኮሬብ በዓለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ ዓለቱንም ትመታዋለህ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱ ይወጣል አለው። ሙሴም በእስራኤል ሽማግሌዎች ፊት እንዲሁ አደረገ» ይላል።

እግዚአብሔር በኮሬብ በዓለት ላይ በመቆም ከባሕርይው ውኃ ማፍለቅ የማይቻለውን ዓለት ውኃ እንዲያፈልቅ አድርጓል።

ዓለቱ ውኃ ካፈለቀ የቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ሥዕል «ወዝ፣ ዘይት እና እንባ» አፈሰሰ ተብሎ መጻፉ ዕውቅ ድንቅ ብለን የአምላክን ሥራ እንድናደንቅ ይጋብዛል እንጂ አይነቀፍም :: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያ እስራኤል ጠጥተው የረኩበትን ዓለት ምንነት ሲገልጥ «ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፣ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ድንጋይ ጠጥተዋልና፣ ያም ድንጋይ ግን ክርስቶስ ነበር» ብሏል (፩ቆሮ. ፲፥፬)። እዚህ ላይ ውኃ አፍሳሹ ዓለት የክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ቀርቧል። በተፈጥሮም ግዑዝ የሆነው ድንጋይ በርካታ እስራኤላውያን የሚገለገሉበትን ውኃ እንዴት ማፍለቅ ቻለ? ብለው ለሚጠይቁ ወገኖች በእግዚአ ብሔር ተአምር ብለን እንመልሳለን።

ከላይ ባቀረብነው አስረጅ መሠረት የቅዱሳት ሥዕላት መናገር፣ ወዝ፣ ዘይት፣ እንባ መፍሰስ እና መንቀሳቀስ በረ ቅዱሳት ሥዕላት የሆነ አቋም ባላቸው ወገኖች ሲነቀፍ ይታያል። ይህንን እግዚአብሔር በግዑ ዛን ነገሮች ላይቀር አድሮ የሚያደርገውን ተአምር ከማድነት ይልቅ የቤተ ኦ...ቲያንን ሊቀውንት ቅዱሳት ሥዕላት ለማስፈራረያነት እንደሚጠ ቀሙበት ለማስመሰል መናፍቃን ሲዘላብዱ «ለሥዕለ ማርያም መስገድ» እንዴት ተቀባይነት አገኘ? በማለት ይጠይቁና ለዚህ ኦፋቂ አዘል ጥያቄ መልስ ሲሰጡ «ምስሎቹ ባሉበት ሆነው ተንቀሳቅሰው የተሊያየን ድርጊት ያደርጋሉ በሚል ማስፈራራት» የሚል መልስ ይሰጣሉ።

፪፮፫. ቅዱሳት ሥዕላትን ሲዳስሱ ይፈሙሳሉ

መናፍቃን ከሚተቹት የተአምረ ማርያም ነቅዕ አንዱ ይህ ነው። አፍርንጊያውም ሥዕሊቱን ይወስዳት ዘንድ እንዳልተቻለው ባወቀ ጊዜ ሾተል ይዞ እጁን በመስኮት አዝልቆ ከሥዕሉ የሥጋ ቁራጭ ያክል ቆረጠ ያን ጊዜ ከሥዕሏ ደም ወጣ። እርሱም የሥጋ ቁራጭ ያክል ይዞ ወጥቶ ተመመረ። ያንጊዜም ሰዎች አውቀው ፈልገው በጭንቅ አግኝተው ያዙት ይገድሉት ዘንድም ወደዱ። ያን ጊዜ እኔን ስለመውደዱ ከብር ሊሆን ወስዷል እንጂ ይህን በክፋት አላደረገውምና ተውት አትግደሉት የሚል ቃል ከሥዕሉ ተንገረ፣ ነገር ግን የተቆረጠውን ሥጋ ከቦ ወስዳችሁ ከተቆረጠበት ቦታ ግጠሙት ያን ጊዜውን አኖ ሩትና ቀድሞ እንደነበረ ሆነ። ያች ሥዕል ሥጋን የለበሰች ትመስላለች ከእርሷም እንባና ወዝ ይወጣ ነበር። ከመዙም የተለዩት ከሚያስጨንቅ ደዌ ይፈወሱ ነበር። ገጽ.114-115።

ይሽንን ተአምር ለመረዳት የእምነት ዐይን ያስፈልጋል። እግዚአ ብሔር ምንም ዓይነት ነገርን ማድረግ እንደሚይሳነው መረዳትን፣ በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ መሆኑን በእርሱ ያመኑ ወገኖች እርሱን እንደሚመስሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን እንደተሰጣቸው /ዮሐ. ፩፥፲፪/ የእግዚአብሔር ልጅም እናት የሆነች ማርያም ይሽንን ሥልጣኗን ተጠቅማ ተአምር እንዳደረገች መረዳትን ይጠይቃል።

በዚህ ተአምር ላይ የቀረበው ተአምር «ለእመቤታችን ሥዕል የተለየ ፍቅር የነበረው ሰው ሥዕሏን መውሰድ ቢሳነው ሾተል ይዞ እጅን አስገብቶ ከሥዕለ ማርያም ላይ ቆርጦ መስዷል። በዚህ ጊዜ ከሥዕለ ማርያም ላይ ደም ወጥቷል። ድርጊቱን ያደረገው ሰው ከተያዘ በኋላ ድርጊቱን የፈጸመው እመቤታችንን ከመውደዱ የተሥነ በመሆኑ ይቅርታ እንዲደረግ ለት እመቤታችን ጥሪ ማቅረቧን ይናገራል እንጂ አያስፈራራም። ይል ቱኑ እንደዚህ ዓይነት በፍቅር ላይ የተመሠረተ ድርጊት ሲደረግ እግዚአ

ብሔር የአማኞችን ፍቅር በማየት ተአምር እንደሚያደርግ በቅዱስ መጽሐፍ በስፋት ተጽፏል።

በተአምረ ማርያም የተጠቀሰው ሥዕለ ማርያምን ከፍቅር የተነሳ የቆረጠው ግለሰብ ድርጊት በሐዋርያት ሥራ ከቅዱስ ጳውሎስ ፈውስ በመፈለግ የአካሉን ልብስ ጨርቅ ቀድደው ድውያን እየወሰዱ ይፈወሱ ነበር› ተብሎ ከተጻፈው አማናዊ ታሪክ ጋር ይዛመዳል /የሐዋ. ፲፱፥፲፪/።

፮.፩.፬. ቅዱሳት ሥዕላት በፈታቸው የሚሰግድላቸውን ያክብራሉ

እግዚአብሔር በባሪያው በቅዱስ ጳውሎስ የአካል ልብስ ተአምር ካደረገ በእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ተአምር ማድረግ አይሳነውም። አንዳንድ ወገኖች በቅዱስ መጽሐፍ ከተጻፈው ተአምራዊ ታሪክ ጋር ተዛምዶ ያላቸው ተአምራት ሲቀርቡ ቤተክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላት ተቀባይነት እንዲያገኙ በማስፈራሪያነት እንደተጠቀመችበት ጽፈዋል። ነገር ግን ከእውነት የራቀ ነው። ምክንያቱም ከላይ የቀረበው ታሪክ በይዘቱ ምንም ዓይነት ማስፈራሪያ የለውምና ነው።

በእመቤታችን ሥዕል ፊት መሰገድ ትሕትና ነው። ለሥዕሏ ባለቤት ያለንን አክብሮት መግለጫ ነው። የአምላክን እናት ሥዕል የሚጠየፍና አክብሮት የማይገልጥ ሰው እንደ ግብር አባቱ ዲያቢሎስ ትዕቢተኛ ስለሆነ እግዚአብሔር ራሱ ትዕቢተኞችን እንደሚቃወም ተጽፏል /ያዕቆ. ፬፥፮/ ትእቢተኞች የሚጠብቃቸው ቅጣት ምን ሊሆን እንደሆነ ተአምረ ማርያም ሲገልጥ

በአስክንድርያ ሀገር ቀልሞን በሚባል ቦታ በእመቤታችን ስም የተሠራች ቤተክርስቲያን ነበረች። የገዳሙ አስተዳዳሪ ሰሉሞን ይባላል። በዚያች ቤተ ክርስቲያንም ካለች ከእመቤታችን ሥዕል ብዙ ተአምር ይደረግ ነበር። የገዳሙም አስተዳዳሪ ለሥዕሏ ሦስት ጊዜ ሲሰግድ ከእርሱ ጋር አራት ሰዎች ነበሩ እርሱን አይተው ሦስቱ ለሥዕሏ ሰገዱ አንደኛው ሰይጣን በልቡ አድሮበት ለድንግል ማርያም ምስጋና ይሁንና የሰው እጅ ለሠራው እንዴት አሰግዳለሁ? ብሎ ተጠራጠረና ቢሥዕሏ ተዘባበተ በዚያችም ሰዓት ምላሱ ተጎልጉሎ ከስንፈሮቹ አንድ ስንዝር ያህል ወጣ።[118]

118. ሊተጠበብት አስራደ ባያብል፣ ግንሌተ ጽጌ። ፲፱፻፷፰/ ገጽ ፶፩-፶፪።

መናፍቃን ግን በመጽሐፉ ላይ በቀጥታ ያልተባለውን «ለእመቤታችን ሥዕል ስላልሰገደ ሞተ» በማለት ለማደናገር ይሞክራሉ። ነገር ግን ከዚህ በተገለጸው መልክ እንደተተረከው ከአራቱ ሰዎች አንደኛው በልቡ አድሮበት «የድንግል ማርያም ሥዕል የሰው እጅ ሥራ እንደተመለከትነው እግዚአብሔር በቅዱሳን አድሮ ትዕቢተኞችን ይቀጣል። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ ሐናንያና ሰጲራ የተባሉ ባልና ሚስቶች ቅዱስ ጴጥሮስን በመዋሸታቸው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ላይ በመዋሸታቸው ተቀስፈው ሞተዋል (የሐዋ. ፭፥፩-፲)። የግለሰቡም ሞት በትዕቢት የመጣ ነው እንጂ ሥዕለ ማርያምን ሰዎች እንዲቀበሉ በሚል ዓላማ የተጻፈ አይደለም።

ሌላው መናፍቃን «መልክአ ሥዕል» ተብሎ ከሚጠራው መጽሐፍ ወስደው ለድንግልናቸ ክልኤ ወሰባት ለሥዕልኪ ቅድመ ገባኤ ዘኢሰገደ ለሥዕልኪ አስራጸ ምሳሌኤ በሥጋሁ ወበነፍሱ ኢይርከብ ትንሣኤ በሁለት ወገን ድንግል ነሽና እሰግድልሻለሁ ለሥዕልሽም በነፍሱም በሥጋውም ትንሣኤ አያግኝ የሚለውን «የእርኪውን ሐሳብ የሚያንጸባርቀውን ቃል ቦግአዙ አቅርበው ወደ አማርኛ ሲተረጉሙ «አስራጸ ምሳኤ፣ ትዕቢት አብቅሎ» የሚለውን አውቀው ገድፈውታል። ይኸውም የአርኪውን ሐሳብ ቆርጠ በማስቀረት ለማደናገሪያ የተጠቀሙበት ስልት መሆኑን እንገነዘባለን። በመልክአ ሥዕል ላይ የቀረበው ሐሳብም በትዕቢቱ እንደተቀሰፈው ሰውዬ «አመጽን አብቅሎ» ሥዕለ ማርያምን የሚቃወም የሥዕሏን ባለቤት እመቤታችንን የሚቃወም የሚኖትና በመሆኑ ዕድል ፊንታው ጽዋ ተርታው ሞት መሆኑን ይናገራል እንጂ ሥዕለ ማርያምን ተተበሉ ብሎ አያስፈራራም።

ስለዚህ በትዱሳት ሥዕላት ፊት የጸጋ ወይም የአክብሮት ስግደት መስገድና መጸለይ ለሥዕሉ ባለቤት ያለንን ከብርና ፍቅር በመግለጽ በረከት እናገኛለን። በተጨማሪ በተአምረ ማርያም ከተመዘገበው ውጪ የሃይማኖት ያልሆኑ የተለያዩ የመንፈስ ብዙኃን ባለሙያዎች በግብጽ እና

በሶርያ ከሥዕለ ማርያም ወዝ ሲፈስ ብርሃን ሲወጣ መዘገባቸውን ከዓለም ዓቀፍ የመረጃ ምንጮችም ተዘግቦአል። እነዚህ ሁሉ ምስክር ነቶች የእግዚአብሔርን ኃይልና የሥጠታውን ባለጠግነት የሚያስረዱ ናቸው።

ለእግዚአብሔር ክብር ይግባውና ቅዱሳት ሥዕላት ኢአማንያን በሚበዙበት ሀገር መንደር ሳይቀር እየተገለጡ ብርሃን እየፈነጠቁ ወዝ እያፈሰሱ ነው። በአርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር የሚገኙ ምእመናን እምነታቸውን እንዲያጸኑ እያደረጉ ነው። ለምሳሌ በቅርቡ በከንባታና ሐዲያ ሀገረ ስብከት በቡሽና ፋበሌ ገበሬ ማኅበር በዛፍ ላይ ሳይቀር ቅዱሳት ሥዕላት መገለጻቸውን የእምነቱ ተከታዩ ያልሆኑ ሰዎች ሁሉ መስክረዋል።[119]

፮.፮ ምስለ ፍቁር ወልዳ

ምስለ ፍቁር ወልዳ /With her beloved son/ ተብሎ የሚጠራው ሥዕል እመቤታችን ከተወዳጅ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላትን የእናትነት ሐላፊነት ያመለክታል። አንዲት እናት ልጇን ታቅፋ እንደም ትታይ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመልአከ ብሥራት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የወንድ ዘር ምክንያት ሳይሆናት የወለደቸውን ልጇን ታቅፋ ትሳላለች።

በምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል በስተግራ ክንፉን ዘርግቶ ሰይፍ ይዞ ይሣላል በስተቀኝ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አበባ፣ ሰይፍ ወይም መስቀል ይዞ ይሣላል። እኒህ ሥዕሎች የሚሳሉት በምሳሌነት ነው።[120] ይህን «ምስለ ፍቁር ወልዳ» ተብሎ የሚጠራውን ሥዕል የሳለው ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመራማሪዎችና ኢትዮጵያውን ቅዱሳን ጸሐፍት በድርሰታቸው ገልጸዋል። ከእነዚህም ውስጥ «ሰላም ለሥዕልኪ፣ እንተ ሰዓላ በዕዱ ሉቃስ ጠቢብ እም ወንጌላውያን አሐዱ፤ ከወንጌላውያን አንዱ ጥበበኛው ሉቃስ በእጅ ለሳለው ሥዕልሽ ሰላምታ ይገባል»[121] የሚለው አንዱ ነው።

119. አቦብ ስቡም፣ «ምሥዕል እድገኖ ቀአምር ለተለያዩ ሰዎች ተንሸራ ስምህ እድቅ። ገጽ ጎጦት ቀጥር ፫፫ ቅጽ፲፮ ቅጥር ያሮዛ ገጽ ፩።
120. አባ ጎርጎርዮስ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፲፯ዕደዛ ገጽ ፻፲፮።
121. ጽኒ ሎጣሁ ገጽ ፻፹። መልክአ ሥዕል።

ወንጌላዊ ቅዱስ ሉቃስ የጌታችን ዜና ልደት ሥዕላዊ በሆነ መንገድ በግርግም መተኛቱን በዕለተ ልደቱ መላእክት የምስጋና መዝሙር መዘመራቸውን እረኞች ባዩት የጌታ ክብር መፍራታቸውን የጻፈ ብዚብ ነው። በወንጌል ሥዕላዊ በሆነ መልክ ያቀረበውን የጌታችንና እና የእናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን ምስለ ፍቁር ወልዳ ታሪክ ሥዕል ሥሉ ማቅረቡ አይደንቅም። ቅዱስ ሉቃስ የተለየ የእጅ ጥበብ የነበረው በሥዕል እና በጽሑፍ ይሰብክ የነበረ ወንጌላዊ በመሆኑ በአረማ ውያን እጅ በወደቀ ጊዜ እንኳን ጣዖት አምላኪው ንጉሥ «የቅዱስ ሉቃስን ቀኝ እጅ መጻሕፍትን እየጻፈች የሮምን መንግሥትና ሕዝብ የምታስት ይህች ናት»[122] በማለት እንዲቆረጥ አድርጓል። የምስለ ፍቁር ወልዳ /እመቤታችን ከተወዳጅ ልጇ ጋር/ ሆና የሚያሳየውን ሥዕል ብዙ የመጻሕፍት አስረጅዎች ሳሉ ታሪክ ያላንበበ አንድ ደፋር አላዋቂ በዝርቡ የራሱን ልብወለድ ፈጠራ ኩጥፈው በተቃራኒ ለማቅረብ ሞክሯል። «የእመቤታችን ምስለ ፍቁር ወልዳ ቅዱስ ሉቃስ ለመሳሉ ማስረጃ የለም» ይላል።

አላዋቂው ጸሐፌ እውነታውን ለመሸፈን ይሄን ይናገር እንጂ ከጌታ እግር ሥር ቁሞ ብሎ የተማረው ሐዋርያው ያዕቆብ ቅዱስ ሉቃስ የእመቤታችንን እና የተወዳጅ ልጇን ሥዕል መሳሉን በወንጌል ጽፏል። ይህን አማናዊ ታሪክ አባ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ ሲያብራሩ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ደግሞ ወላዲተ አምላክ በነበረችበት ኑፍለ ዘመን የነበረው ሐዋርያው ያዕቆብ የጌታን ታሪክ /ወንጌል/ ሲጽፍ ስለ ወላዲተ አምላክ ብዙ ጽፎአል። በዚህ የያዕቆብ ወንጌል /ዮያዕቆብ ታሪክ/ በተባለው የትውፊት መጽሐፍ ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ለመጀመሪያ ጊዜ የማርያምን ሥዕል መሣሉ ተጽፎአል ብለዋል።[123]

መናፍቃን ለምን ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ሔዱ የሚል ጥያቄ የለንም አውቆ የተኛን ሰው ቢቀሰቅሱት አይሰማምና። ከዚህ አኳያ ቅዱሳት ሥዕላት በተለይም ምስለ ፍቁር ወልዳን የተሳለበትን ዘመን በጥበብ ገፍተው እነርሱ መነሻችን ወደሚሉት ዘመን ሊያጠጋጉት ሲንደፋደፉ

122. ትርጓሜ ገድለ ሐዋርያት። ገጽ ፻፫፭-፻፫፮።
123. አባ ገብርኤልገንዜ ቅዱሳን ገጻሊስ አዘነ በቀደሙገጽ ፻፲፩።

ይታያል። ነገር ግን በየትኛውም ዘመን ይሣሉ መልእክት በማስተላለፍ ቀጥተኛ ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ይችላል።

የተአምረ ማርያም ጸሐፊንም «ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ» መሆኑን ጠቅሰዋል። ይህም ትልቅ ሐሰት ነው። የተአምረ ማርያም ጸሐፊ የጥር ጥልያ ሀገር ኤጲስ ቆጶስ የነበረ ይትሰዮስ የሚባል ሰው እንደጻፈው ተአምረ ማርያም ይገልጣል።[124] በእርግጥ ንጉሡ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በዘመኑ ከላይ በተገለጠው ኤጲስ ቆጶስ የተጻፈውን ተአምረ ማርያምን ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ማስተርጐሙ ይነገራል። ይህን እውነት ከደና ገልብጠ «ምስለ ፍቱር ወልዳ የተባለው ሥዕል ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ሣለው ብሎ ተአምረ ማርያም ውስጥ ያስገባው ዘርዐ ያዕቆብ ነው» ማለት ተራ አሳዋቂነት ነው፤ መረጃ የለውም።

ከዚህ በተጨማሪ ጌታችን በተወለደ በስምንተኛው ቀን እመቤታችን ሁለት ርግብ ይዛ ወደ ቤተ መቅደስ መሔዷን መናፍቁ በተሳሳተ መልኩ ጽፏል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለትሕትና ያደረገውን ወይም የፈጸመውን ሕግ ሲያብራራ «ጊዜው ግን በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ሰደደ ከእመቤታችን ተወለደ፣ ሕገ አራትን ሲፈጽም አደገ፣ በአራት ያሉትን ወደ ወንጌል ይመልሳቸው ዘንድ» ብሏል (ገላ. ፬፥፬-፭)። የእኛ እምላክ የሁሉ ጌታ ሠራጌ ሕግ ከሠሌ ኩሉ፣ ሁሉን ቻይ ሲሆን ወደዚህ ዓለም ለልሰልና ሳይሆን ለትሕትና ስለመጣ ሕግ ጠብአያዊና ሕግ መጽሐፍዊን ፈጽሟል። ሕግ ጠብዓያዊ የሚባለው ግእዘ ሕፃናትን አለማፋለሱ ነው። በሌላ አነጋገር ሥርዐተ ሕፃናትን ሳያፋልስ፣ ማለት አምላክ ነኝ እና ዕለቱን ልደግ ልመንደግ ሳይል ቀስ በቀስ ማደጉን ያመለክታል። ይህንን ጌታችን አድርጐታል። ሌላው በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ እንደተገለጸው «በአራት ውስጥ ያሉትን ወደ ወንጌል ይመልሳቸው ዘንድ ሕገ አራትን ፈጽሟል።»

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ሕገ አራትን መፈጸማቸው ለትሕትና ለአብነት እንጂ፣

124. ተአምረ ማርያም፣ «በእንተ ደቅስዮስ» ገጽ ፩፻፱።

ከሥርዐተ ፍጻሜ በኋላ ከማስተማር የዘለለ አንዳች የሚያገኙትን ነገር የለም። ትልቁ ቁም ነገር ጌታ ቀድሞ በረድኤት በነቢያት አድሮ የሠራውን ሕግ መፈጸሙ ነው። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአራት ሕግ እንደሚያዘው የርግብ ጫጩቶች ይዛ መቅረቧ ሕጉን ለመፈጸም ያህል እንጂ፣ በሌሎች ሴቶች ልማድ አይደለም። ወንጌላዊውም «የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ፣[125] ያለው በሌሎች ሴቶች ልማድ ለመናገር እንጂ በእመቤታችንስ የመንጻት ጣጣ የለባትም።

መናፍቃን የእመቤታችንንም ክብር ለማጉደፍ የሚችሉ የመሰላቸው መጻሕፍት ያላሉትን ቀጣጥለው ከልቡናቸው አንቅተው ይጽፋሉ። የጽሑፋቸው ደራሲም ተንኮል አቀናባሪው ሰይጣን ነው ። «ከላይ አስቀድመን እንደ ገለጽነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለትሕትና ወደዚህ ዓለም ስለመጣ በእርሱ ምክንያት ሌሎች አንዳይሰናከሉ የመንግሥት ግብር ሁሉ ከፍሏል (ማቴ. ፲፯፥፳፯)።

እመቤታችን ከጊታችን ጋር ጫጩት ይዛ ወደ ቤተ መቅደስ መሄዱ ሕግን ለመፈጸም እንጂ በመፈጸሟ የሚደረግላት ወይም የምታገኘው ነገር ኖሮ አይደለም። ይህን እመቤታችን ለትሕትና ያደረገችውን ነገር አንዳች ነገር የሌላት ድኻ ሴት አድርጉ ለማቅረብ ይጠቀሙበታል። እከብር አይል ክቡር እጸድቅ አይል ጻድቅ እንግሥ አይል ንጉሥ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችውን እመቤታችንን በዚህ ዓለም ሰዎች ከልጇ እግኝተው በሚከብሩበት ምድራዊ ጥሪት መገመቱ አላዋቂነቱን ያሳያል። ባላዋቂነት ላይ ኑፋቄ ሲጨመር ጨለማውን እስቡት።

መናፍቁ ለቤተ መቅደስ ሁለት ጫጩቶች ከሰጠች ለምን ቢሥሏ ላይ የወርቅ ልብስ ተጐናጽፋ ትሣላለች? የሚል መከራከሪያውን ሲያቀርብ ስለ ከበረ ወንበር የወርቅ ፊርጥ የሐር መጐናጸፊያ ወርቀ ዘቦና የወርቅ አክሊል እንሥቷል። እመቤታችንን በነበረ ወንበር የወርቅ ፊርጥ ያለበት መጐናጸፊያ ወርቀ ዘቦና የወርቅ አክሊል ደፍታ መሣሏ የሚያስተና ወይም የሚያስነሱ ጉዳይ አይደለም። እንኳን የሰማይና የምድር ጌታ እና ንጉሥ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ይቅርና የምድራውያን ነገሥታት

125. ትርጓሜ ወንጌል ቅዱስ ዘሉቃስ ፲፱ኛው ምዕራፍ ገጽ ፫፻፳፰።

እናቶች የወርቅ ልብስ ለብሰው አክሊል ደፍተው ፎቶ መነሣታቸውን በሥዕል መሳላቸው ጸሐፊው በታሪክ መጻሕፍት አልተመለከተ ይሆንን? እመቤታችን በምድራዊ የወርቅ ልብስ እጠት መገጠቱ እንዴት ያሰኛል።

በምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል እመቤታችን የወርቅ መጐናጸፊያ ለብሳ መሳሉ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ነው። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ከብረ ድንግልን ሲገልጥ «በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች» ብሏል» (መዝ. ፵፬፡፱)። የሁለቱ መላእክት ከገሬና ከቀኝ መሣል ጌታ ሲወለድ በቤተልሔም የተከናወነውን መንፈሳዊ ዜናን ያስታውሳል።

ቅዱሳት ሥዕላት በመሠረቱ /Religious symbols/ እንደመሆናቸው በተጥታ ቅዱሳንን እንዲመስሉ ወይንም እንዲያክሉ አይጠበቅባቸውም። እነርሱ /ቅዱሳን/ በነበሩበት ዘመን የፎቶ ባለሙያ ቀርቦ የሚያንሣቸው አይደለም። የሆነው ሆኖ መናፍቃን ለማደናገር ግምታዊ የሆነውን መላ ምታቸውን ይናገሩ እንጂ። ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል እመቤታችን በዐሥራምቹ የዕድሜ ክልል የምትገኝ ሴት ሥዕል አምሳል መሣሏ ይታወቃል። ሥዕሏ ከዚህ ከፍ ብሎ ቢሣል እንኳ እርሷም ለጇም ቀስ በቀስ የሚያድግ አካለ ሥጋ መያዛቸው መዘንጋት የለበትም።

እዚህ ላይ መናፍቃን ምን ዓይነት ዝንጋዔ ልቡና አድሮባቸዋል? ያሰኛል «ማርያምና ክርስቶስ የተነሡት አማናዊ ፎቶ» ብለው መጻፋቸው ምን ዓይነት ድንቁርና ነው። በዚያ ዘመን ሥዕል ማሣል ቢኖርም የፎቶ ግራፍ ፕበብ አልነበረም። ፎቶ ካሜራ በቅርበ የመጣ የፈጠራ ውጤት መሆኑ አገር ያወቀው እውነት ሆኖ ሳለ «ማርያምና ክርስቶስ የተነሡት አማናዊ ፎቶ ነውን» ብሎ መጽሐፉ ጸሐፊው የሚናገረውን ያጣ ያስመ ስለዋል። በመሠረቱ ጸሐፊው በገለጸው መልክ የተሣለው ምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕለ የለም። ዐይናቸውን አተልቶ አፍንጫቸው አስረዝሞው የሚሣሉት ቅዱሳት ሥዕላት የራሳቸው መንፈሳዊ ትርጉም አላቸው።[126]

መናፍቃን በመጨረሻ ያነሡት የሥዕለ ማርያም ነተና ደግሞ የሚከተለው ነው «ሴላኛው» «የማርያም ሥዕል» ደግሞ በእንዝርት ጥጥ ሰትፈትል

126. እንዲህም ያለ ግንባቤ ነቅዐ ሕይወት፣ ገጽ ፩፻፴።

የሚያሳየውን ብንመለከት ይህ የቤት ተግባር የኢትዮጵያውያት እናቶች ተግባር ወይስ የእስራኤላውያት ባሕል? መልሱን ለአንባቢ እንተዋለን» ብለዋል። ገጽ 122

ጸሐፊው የነተፈው ሥዕል በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም ትምህርት መሠረት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ጌታችንን እንደምትፀንስ እመቤታችንን ያበሠራት በቤተ መቅደስ ሐርና ወርቅ እያስማማች በምትፈትልበት ጊዜ ነው። ታዲያ ይህ ሥዕል የነገረ ማርያምን አስተምህሮ ስለሚያንጸባርቅ እመቤታችን ወርቅና ሐር እያስማማች ስትፈትል የሚያሳይ ሥዕል በጣና ሐይቅ ዘጌ ውስጥ ዑራ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንና በሌሎችም ገዳማትና አድባራት ይገኛል። ይህ ሥዕል ትክክለኛውን የነገረ ማርያም አስተምህሮ ስለሚያንጸባርቅ ብቻ በጸሐፊው መነሳቱን ከአንባብያን አይሰወርም። ኢትዮጵ ያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም የጌታችንን ዜና ብሥራት ሲሰብክ «ወእንዘ ትፈትል ወርቀ ወሚሳተ አስተርአያ ገብርኤል ግብተ፡ ወርቅና ሐር እያስ ማማች ስትፈትል ገብርኤል ታያት» ብሏል።

በአጠቃላይ መናፍቁ ጸሐፊ ቅዱሳት ሥዕላትን ከአረማውያን ጣዖታት ጋር በማመሳሰል ኑፋቄውን ለማስተላለፍ ሞክሯል። እግዚአብሔር ፊቃዱ ሆኖ በጽላተ ኪዳኑ ላይ እንዲሣል የፈቀደውን ሥዕል፡ ቅዱሳን ሐዋር ያት በሐዲስ ኪዳን «ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል» ሲሉ አጠናክረውታል /ገላ ፬፡፲፱/።

እኛ ግን እግዚአብሔር በሠራልን ሕግ መሠረት ለቅዱሳት ሥዕላት ተገቢው ክብር እንሰጣለን። ይህን በማድረጋችን ለቅዱሳኑ ያለንን ፍቅር አክብሮት እንገልጻለን።

መናፍቁ ጸሐፊ ግን እግዚአብሔር በዚህ እየተገለጽኩ አኔጋግርሃለሁ ሲል የሰጠውን ታቦተ ኪዳኑን ከቅዱሳት ሥዕላት ጋር አያይዞ ሲንቅና ይሁን እንጂ ለሚመጣው ለክርስቶስ አገልግሎት ትንቢት ሰጪ የነበረው ታቦትና ኪሩቤል ክርስቶስ በአካል ሲመጣ እንደሚቀር በአዚዩ በኤርምያስ እንደተተነበየ ልብ አያደርጉ ትም አያስቡትምም አይሹቱምም ከእንግዲህ አይደግምም ብሏል። እርሱ ጥቅሱን ጠምዝዞ ሊደባለቅ የፈለገውን ሐሳብ

ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይዘጋዋል። ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሔድ አትጠመዱ ጽድቅ ከዓመጽ ጋር ምን ተካይፋነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔርን ታቦትንስ ጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖረው ማን ነው? (፪ኛ ቆሮ. ፮፡፲፬) ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህ ምስጢር ተሰውሮት ይሆንን? ነው ወይንስ እነ ሰሎሞን እንደለመዱት ድፍረታቸው ቅዱስ ጳውሎስን ያሳናገረ መልአክ ተገለጠላቸው? ባጭሩ የአረማውያን ጣዖት ከሥዕልና ከታቦት ጋር አደባልቆ ማስተማር አይቻልም።